# Ordo Salutis/ order of salivation

Ordo salutis የላቲን ቃል ሲሆን ትርጉሙም "order of salivation" ወይንም የድነት ቅደም ተከተል ማለት ነዉ። ከእርሱ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላ Concept ደግሞ historia salutis ሲሆንይህም የላቲን ቃል ትርጉሙ" the history of salvation "ወይንም የድነት ታሪክ ልንለው እንችላለን ። በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው ? historia salutis እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ ለመቤዠት ያደረገውን ወይንም የሠራቸውን ክንውኖች የሚያብራራ ሲሆን Ordo Salutis ደግሞ የቤዛነት ስራዎች ውጤት ለግለሰብ የሚተገበርበትን ቅደም ተከተል ያብራራል ። በእዚህኛው ፅሁፍ ትኩረት የምናደርገው በordo salutis (የድነት ቅደም ተከተል ) ላይ ይሆናል

1.ቅድመ ድንጋጌ (Predestination) ፣ 2.ጥሪ (Calling) ፣ 3.ዳግም ውልደት (Regeneration) ፣ 4. ንሰሃ እና እምነት Repentance and Faith (conversion) ፣ 5. መፅደቅ (Justification) ፣ 6. ልጅነት (Adoption) ፣ 7. መቀደስ (Sanctification) ፣ 7. የቅዱሳን ፅናት (Perseverance and Preservation) ፣ 9.መክበር (Glorification) ። እነዚህ topics በዋናነት የሰው ሁኔታ በንፅህና ፣ በውድቀት ፣ በፀጋ እና በክብር እንመለከታለን ። የዛሬውን ትምህርት የመጀመሪያው የሆነውን predestinationንን እንመልከት ።

**– <u>ቅድመ ድንጋጌ (Predestination)</u>**

ይህንን topic አብዛኛው ሰው በመዝሙር የሚቀበለውና የሚባረክበት ሲሆን ፣ ዶክትሪን ሲሆን ግን የሚቃወመው topic ነው ። ሳልወድህ የወደድከኝ ፣ ሳልመርጥህ የመረጥከኝ የሚለውን የተሰፋዬ ጫላን መዝሙር እየዘመረ ፣ የመረጥከኝ ተባረክልኝ የሚለውን የአገኘው ይደግ መዝሙር እየዘመረ unconditional election ስትለው ይቃወምሀል ። ይህንን የተዛባ ምልከታ አስቀድሞ ማጥራት ያስፈልጋል ።

**– ምርጫን በተመለከተ ብዙ የተለያዩ ምልከታዎች አሉ ።**

ሁሉም አማኝ ምርጫን ይቀበላል ። ግን ደግሞ ምርጫን በተመለከተ ያለው የሰነ መለኮት ምልከታ የሰነመለኮት ልዩነቶችን ፈጥሯል ። እነዚህ ምልከታዎች ፦ 1ኛ, እግዚአብሔር ለአገልግሎት እንጂ ለድነት አልመረጠም የሚሉ 2ኛ, እግዚአብሔር ለአገልግሎትም ለለድነትም ይመርጣል ግን ለድነት ሲመርጥ በግለሰብ ደረጃ ሳይሆን እንደ ማህበር (corporate) ነው የመረጠው የሚሉ 3ኛ, እግዚአብሔር ግለሰቦችን መርጧል ግን የሚድኑትን ብቻ ነው ለድነት የመረጠው የሚሉ ( single predestination). 4ኛ እግዚአብሔር ሲመርጥ ለድነትም ፣ ለጥፋትም ነው የሚመርጠው የሚሉ ( double predestination)q. 5ኛ, ለድነትም ለጥፋትም ይመርጣል ነገርግን ሁለቱም ላይ positive positive ነው ምርጫው የሚሉ ማለትም ፦ ለድነት የተመረጡት ላይ እግዚአብሔር ማመን እንዲችሉ Actively እንደሚሰራ ለጥፋት የተመረጡት ላይም እንዳያምኑ Activity ይሰራል የሚሉ አሉ ። እነዚህ Hyper Calvinist ይባላሉ ። 6ኛዉ ለድነትም ለጥፋትም ይመርጣል ነገርግን ሁለቱም ላይ positive Negative ነው የሚሰራው ። ማለትም ፦ ለድነት የተመረጡት ላይ እግዚአብሔር ማመን እንዲችሉ Actively ይሰራል ። ለጥፋት የተመረጡት ላይ ደግሞ Passively ይሰራል የሚል ነዉ። ይህን Reformed view እንለዋለን።

**– መፅሐፍ ቅዱስ ስለምርጫ ምን ይላል ?**

አስቀድሞ መመረጥን ስናስብ በቅድሚያ መነጋገር ያለብን ጉዳይ እግዚአብሔር ሰራውን ሲሰራ እንዴት ነው የሚሰራው ? የሚለውን ነው ። በዘፈቀደ ነው የሚሰራው ወይንስ በእቅድ ? የትኛውም አማኝ እግዚአብሔር ያለ ዕቅድ በእቦ ሰጥ ነው የሚሰራው የሚል የለም።

እግዚአብሔር ሲሰራ የሚሰራው ሁሉን በዕቅዱ መሰረት ነው ። ይህንን በኤፌሶን መፅሐፍ ላይ መመልከት እንችላለን ። — ኤፌሶን 1፥11 (አዲሱ መ.ት) ። "ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሠራው እንደ እርሱ ዕቅድ አስቀድሞ የተወሰንን እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል፤"

ይህ ማለት እግዚአብሔር በዕቅድ ነው የሚሰራው ደግሞም ያለ ዕቅዱ የሚሆን አንዳች ነገር የለም እያለን ነው ። ከእዚህ ጋር ተያይዞ አንድ ማንሳት ያሉብን ጥያቄ እነዚህ የእግዚአብሔር እቅዶች ወደ መሆን የሚመጡት እንደሚሆኑ ስለሚያውቅ ነው ? ወይንስ እንዲሆኑ ስለወሰነ ነው ?

የሚሆኑት ነገሮች እንደሚሆኑ ስለሚያውቅ ነው የሚሆኑት ካልን አቀደ ፣ ወሰነ ብለን መስማማት የለብንም ። ምክንያቱም እግዚአብሔር አቃጅ አምላክ ነው ብለን ከተሰማማን በተዘዋዋሪ ነገሮቹ በየት በኩል መስመር መያዝ እንዳለባቸው ወስኗል እያልን ነው ። ስለዚህ ሊሆን የሚችለው ሁሉም ነገሮች ወደመሆን የሚመጡት እንዲሆኑ ስለወሰነ ነው ። ይህም የእግዚአብሔርን ሉአላዊነት በቀጥታ የሚመለከት ነው ። **እግዚአብሔር ሉአላዊ ነው ስንል እስያልን ያለነው ፦ ከእሱ ዕውቀት እና ከእርሱ ቁጥጥር ውጪ የሆነ አንዳች ነገር የለም ። ሁሉንም በሥልጣኑ ቃል ይቆጣጠራል። ከግዑዝ አካል እስከ ሰብዓዊ ፍጡር መላው አጽናፈ ዓለም ውስጥ ያሉ ነገሮች ከእርሱ በታች ናቸው ማለታችን ነው ።**

–ዳንኤል 4፥35 (አዲሱ መ.ት) ። "የምድር ሕዝቦች ሁሉ፣ እንደ ኢምንት ይቈጠራሉ፤ በሰማይ ኀይላት፣ በምድርም ሕዝቦች ላይ፣ የወደደውን ያደርጋል፤ እጁን መከልከል የሚችል የለም፤ 'ምን ታደርጋለህ?' ብሎ የሚጠይቀውም የለም።"

– ኢሳይያስ 46 ⁹ የጥንቱን፣ የቀደመውን ነገር አስታውሱ፤ እኔ አምላክ ነኝ፤ ከእኔም በቀር ሌላ የለም፤ እኔ አምላክ ነኝ፤ እንደ እኔ ያለ የለም።¹⁰ የመጨረሻውን ከመጀመሪያው፣ ገና የሚመጣውንም ከጥንቱ ተናግሬአለሁ፤ 'ዐላማዬ የጸና ነው፤ ደስ የሚያሰኘኝንም ሁሉ አደርጋለሁ' እላለሁ።

– እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንደ ወደደው እንደ ፈቃዱ የሚያደርግ ከሆነ ይህ ነገር ድነትንም የሚያካትት ነው ?

መልሱ አዎ ነው ። — 2ኛ ተሰሎንቄ 2፥13 (አዲሱ መ.ት) ። "በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፤ እኛ ግን ሁል ጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ይገባናል። ምክንያቱም እግዚአብሔር እናንተን ከመጀመሪያ እንሥቶ በመንፈስ ተቀድሳችሁና በእውነትም አምናችሁ እንድትድኑ መርጦአችኋል።"

**–ኤፌሶን 1፡5 "በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን ።"** ይህንን ልጆቹ እንሆን ዘንድ መረጠን የሚለው ከድነት ጋር እንደ ተያያዘ በሁለት ምክንያቶች መመልከት እንችላለን ። 1ኛ, **በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ** በሚለው መረዳት እንችላለን ። የክርስቶስ ኢየሱስን ስራ ቀጥሎ ባሉት ምዕራፎች የሚያብራራው ለድነት የሆነውን ስራ ነው ። ማለትም ከአብ ጋር ጠላቶች የሆንን ሰዎች በክርስቶስ በኩል ዕርቅን ማግኘታችንን የሚያመለክት ነው ። 2ኛ ልጅነት በራሱ የተብራራው ከድነት ጋር ስለሆነ ። **ኤፌሶን 5 (አዲሱ መ.ት)¹ እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን ምሰሉ፤ ² ክርስቶስ እንደ ወደደን ራሱንም ስለ እኛ መልካም መዐዛ ያለው መባና መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር እንደ ሰጠ እናንተም በፍቅር ተመላለሱ።** ከእነዚህ የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ተነስተን እግዚአብሔር ሰዎችን ለድነት መርጧል ማለት እንችላለን ።

## ምርጫ ለዘላለም ህይወት ብቻ ነው ? ወይንስ ለዘለአለም ጥፋትም ነው ?

ምርጫዉ

ለሁለቱም ነው ። በጣም ብዙ ሰዎች ስለምርጫ ሲነሳ አይረብሻቸውም ነገርግን በሁለተኛው ጎኑ ያለውን ማለትም ለዘላለም ሞትም ተመርጠዋል የሚለውን ሲሰሙ የመጀመሪያውን ጭምር መቃወም ይጀምራሉ ። ግን ሰዎች ለዘለዓለም ህይወት ተመርጠዋል ካልን በተመሳሳይ መንገድ ለዘለአለምም ሞት ተመርጠዋል ማለታችን ነው ። መመረጥ እንዱ ያለአንዱ ትርጉም የለውም ። የሚተው ከሌለ መምረጥ ትርጉም የለውም ። ሁለቱም በአንዴ ነው የሚከሰቱት ፣ ሁለቱም ከዘለዓለም አንድነት ቀን አላቸው ። አንድ ወንድ አንድን ሴት ለትዳር ከመረጠ ያለመረጣቸው ብዙ ሴቶች አሉ ማለት ነው ። እዚህ ጋር negative inference fallacy አይሰራም ። ለምሳሌ ፦ እኔ ሐዋሳ ነኝ ማለት አዲስ አበባ አይደለሁም ማለት ነው ። መመረጥ በውስጡ አለመመረጥን ያቅፋል ።

ይህንን እውነታ ከመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማግኘት እንችላለን ? አዎ ነው መልሱ ። — 1ኛ ጴጥሮስ 2፥8 (አዲሱ መ.ት) ። “ደግሞም፣ “ሰዎችን የሚያሰናክል፣ የሚጥላቸውም ዐለት ሆነ።” የሚሰናከሉት ቃሉን ባለመታዘዛቸው ነው፤ የተመደቡት ለዚህ ነውና።”

ያያዕቆብ ወንድም የሆነው ይሁዳ ስለነዝህ ሰዎች በመልእክቱ አሥፍሯል – "ከረጅም ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ አንዳንድ ሰዎች ሾልከው ወደ እናንተ ገብተዋልና፤ እነርሱ ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌላቸው፣ የአምላካችንን ጸጋ በርኩሰት የሚለውጡና እርሱ ብቻ ልዑል ገዣችንና ጌታችን የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚክዱ ናቸው" ይሁ 1፥4። ስለእነዚህ ሰዎች ሲገልጽ "ከረጅም ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ" ብሏቸዋል። ይህም ረጅም ግዜ ተብሎ የተገለጸው ምን ይሆን? በሁለት መንገድ ትርጉም ተሰጥቶበታል ።

1, ለፍርድ ከፍጥረተ ዓለም አስቀድሞ የተወሰኑ "ምርጦች" ሲሆን ። 2, ወይንስ ከብሉይ ኪዳን ጊዜ ጀምሮ ሀሰተኞች ፍርድ እንደሚገባቸው እየገለፀ ነው የሚል ነው ። ሁለተኛው አገላለጽ ዕብራውያን 1 ላይ ይመስላል ። ዕብራውያን 1፥1 (አዲሱ መ.ት) ። “እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በተለያየ ጊዜና በልዩ ልዩ መንገድ በነቢያት በኩል ለአባቶቻችን ተናገሮ፣”

የተሻለው የሰነ አፈታት መንገድ ለፍርድ እንደተወሰኑ ማመን ነው ። ብሉይ ኪዳን ላይ ሐሰተኛ አስተማሪዎች እንደሚነሱ የተነገረ ነገር አለ ? የሚል ጥያቄ ይነሳል ። መልሱ የለም ነው ። በእርግጥ የእግዚአብሔር እውነት ባለበት በተቃርኖ የሚነሱ ስህተቶች እና አሳቾች እንዳሉ እናውቃለን ። ነገርግን በብሉይ ኪዳን ይህንን አሰመልክቶ Precisely የተነገረ ትንቢት የለም ። ጆን ጊል እንደሚለው በእዚህ ጉዳይ ላይ በብሉይ የተፃፈ አንድም ነገር አናገኝም ይላል ። ሰለዚህም ፦ ይሄ የሚናገረው የሚጠፉ ሰዎች ከዘላለም በፊት የተወሰኑ መሆናቸውን ነው ይላል ጊል ።

– ሮሜ 9 (አዲሱ መ.ት) ። ²¹ ሸክላ ሠሪ፣ ከሚሠራው ጭቃ፣ አንዳንዱን ሸክላ ለክብር፣ ሌላውን ደግሞ ለተራ አገልግሎት የማድረግ መብት የለውምን? ²² እግዚአብሔር ቍጣውን ለማሳየት፣ ኀይሉንም ለማሳወቅ ፈልጎ የቍጣው መግለጫ የሆኑትን፣ **<u>ለጥፋትም የተዘጋጁትን</u>** እጅግ ታግሦ ቢሆንሳ!

የእዚህን ቁጥር ሀሳብ በትክክል ለመረዳት ቃላቶቹን በጥንቃቄ እንመልከት ። ቁጣ የሚለውን ምዕራፍ 1:18 ፣ 2:5 እንዲሁም 5:9 ላይ እናገኛለን ። ቁጣው ከምን ጋር ነው የተያያዘው ? — ሮሜ 1፥18 (አዲሱ መ.ት) ።“በክፋታቸው እውነትን ዐፍነው በሚይዙ፣ በዐመፃቸውና በክፋታቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣል፤”

— ሮሜ 2፥5 (አዲሱ መ.ት) ። “ነገር ግን በድንዳኔህና ንስሓ በማይገባ ልብህ ምክንያት ትክክለኛ ፍርዱ ሲገለጥ በእግዚአብሔር የቍጣ ቀን በራስህ ላይ ቍጣን ታከማቻለህ።”

— ሮሜ 5፥9 (አዲሱ መ.ት) ። “አሁን በደሙ ከጸደቅን፣ ይልቁንማ በእርሱ በኩል ከእግዚአብሔር ቍጣ እንዴት

እንድንም!"  ይህ ቁጣ ከሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ ጋር በመዛመዱና ለእዚህም የተመደቡ አሉ በማለቱ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ነው ብለን ልንቀበል ይገባል።  ለኩኔነ ወይንም ለፍርድ መመረጥ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ነው። እግዚአብሔር ጻድቅ፥ ቅዱስ፥ ሉዓላዊ አምላክ በመሆኑ የወደደውን ከመለኮታዊው ባሕርይ ተነስቶ ሊፈጽም ይችላል።  ይህም እነርሱ በሌሉበት ሥፍራ እንድንዱን ለድህነት፥ ሌላውን ለጥፋት ማድረግ ይችላል።  እኛ ቤለለንበት ሥፍራ በአንዱ አዳም በደል ኃጢአተኞች ሁነናል፥ ደግሞም ፈጽሞ በለለንበት ሥፍራ በክርስቶስ ጻድቃን ተደርገናል ሮሜ 5፥15-21 እግዚአብሔር ሰዎች በለሉበት ሥፍራ በአዳም በኩል ኃጢአተኛ ካደረጋቸው፥ ሰዎች ባልተሳተፉበት በክርስቶስ ኢየሱስ ሥራ ጻድቃን ካደረጋቸው፥ ሰዎች በሌሉበት ሥፍራ እንዴት ለጥፋት አይመርጣቸውም?  ሰዎች በሌሉበት ሥፍራ እንዴት ለድነት አይመርጣቸውም? ፣ እውን ይህንን ማደርግ አይችልምን? ፣ ሉዓላዊነቱስ ዓለይደልም? ፣ ይህንንስ በማድረጉ ከለሎች መለኮታዊ ባሕርይዎች ጋር ተጣርሷልን?

**– የምርጫ አስተምህሮ ወንጌል መሰበክን ይከለክላል ?**

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር አስቀድሞ ሰዎችን ከመረጠ ወንጌል ለምን እንሰብካለን? ፣ የተመረጡ ሰዎች መዳናቸው አይቀርም ይላሉ ። ይህ የምርጫን አስተተምህሮ በትክክል ካለመረዳት የሚመጣ ጥያቄ ነው ። የምርም አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ምርጫ በትክክል ከተረዳ የወንጌል መልእክት እንዲሰፋፋ ኃይልን ያገኛል። ለምሳሌ፦ በአደገኛ ሰደት መካከል ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው ጽሁፍ ላይ ይህንኑ እናያለን። "    "ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን መዳን ከዘላለም ክብር ጋር እነርሱም ያገኙ ዘንድ፣ ለተመረጡት ሰል ሁሉንም በመታገሥ እጸናለሁ።"( 2ኛ ጢሞቴዎስ 2:10 )  ሰለ ምርጫ አስተምህሮ ትክክለኛ ግንዛቤ ወንጌላዊነትን ያበረታታል ለውጤቱም ዋሰትና የሚሰጥ ነው።

ኃይሉ በወንጌል መልእክት እና በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ ላይ ያለ እንጂ በራሳችን ደካማ አቀራረብ ላይ እንዳልሆነ እናውቃለን ።   አንድ ሰው መመረጡን ወይም አለመመረጡን ለመረዳት መጣር  ይህ የእኛ ጉዳይ አይደለም!! ንስሃ ለሚገባ እና በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ የመዳን ተሰፋ ሁል ጊዜ አለ። እግዚአብሔር በጎቹን ወደ ራሱ ለመሳብ እንደሚጠቀምበት በማወቅ የወንጌል መልእክት ለሰዎች ሁሉ መሰበክ አለበት። እንዲያውም ምርጫን የማይቀበል ሰው ወንጌልን ለመሰበክ እንዴት ሊነሳሳ ይችላል ? ምክንያቱ ሰው ወንጌሉን መቀበል የሚችልበት ኃይል በውሰጡ ሰለሌለው ።  — ዮሐንስ 3፥32 (አዲሱ መ.ት) ። "ያየውንና የሰማውን ይመሰክራል፤ <u>ነገር ግን ምስክርነቱን ማንም አይቀበልም</u>፤" ማንም አይቀበልም የሚል ተሰፋ የሚያሰቆርጥ ነገር እያለ እንዴት ለመሰበክ Motivation እናገኛለን ?

— 1ኛ ቆሮንቶስ 2፥14 (አዲሱ መ.ት) ። "መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው ከእግዚአብሔር መንፈስ የሆነውን ነገር ሊቀበል አይችልም፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለው ነገር ለእርሱ ሞኝነት ነው፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ፣ <u>ሊረዳው አይችልም</u>።"

ሁሉም ሰው ክርስቶስን ከማመኑ በፊት ፍጥረታዊ ሰው ብቻ ነው ። እናም ይህ መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው መንፈሳዊ የሆነውን ነገር ሊቀበለው አይችልም ይላል ። ይህ ድምዳሜ ሲሆን ምክንያቱ ደግሞ ሊረዳው ሰለማይችል ነው ። ሰለዚህ ምርጫ አስፈላጊ ነው ። ለእዚህም ነው እግዚአብሔር የጠራቸው ሰዎች ነው የእግዚአብሔርን ወንጌል መቀበል የሚችሉት የሚለው ።1ኛ ቆሮንቶስ 1 (አዲሱ መ.ት) [18] የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉ ሞኝነት ነው፤ ለእኛ ለምንድን ነው ግን የእግዚአብሔር ኀይል ነው፤ [19] እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤ "የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ፤ የዐዋቂዎችንም ዕውቀት ከንቱ አደርጋለሁ።" [20] ጠቢብ የት አለ? ሊቅስ የት አለ? የዘመኑስ ፈላሰፋ የት አለ? እግዚአብሔር የዓለምን ጥበብ ሞኝነት አላደረገምን? [21] ከእግዚአብሔር ጥበብ የተነሣ ዓለም በገዛ ጥበቧ እግዚአብሔርን ማወቅ ስለ ተሳናት፣ በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ያድን ዘንድ የእግዚአብሔር በጎ

ፈቃድ ሆኖአል። ²² መቼም አይሁድ ታምራዊ ምልክትን ይፈልጋሉ፤ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ፤ ²³ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ መሰናክል፣ ለአሕዛብ ደግሞ ሞኝነት ነው። ²⁴ እግዚአብሔር ለጠራቸው ግን፣ አይሁድም ሆኑ ግሪኮች፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኀይል፣ የእግዚአብሔርም ጥበብ ነው።

# Regeneration

የ Regenerationንን ምንነት ከማየታችን በፊት የቃሉን ትርጉም እንመልከት ። ምክንያቱም የቃላት ትርጉም አንድን ሀሳብ በአግባቡ ለመረዳት ስለ ሚያግዙ ።

**– ፓሌንጄኔሲያ**

በአዲስ ኪዳናችን ላይ ይህ ቃል ሁለት ጊዜ ተጠቅሶ እናገኛለን ። — ማቴዎስ 19፥28 (አዲሱ መ.ት) ። “ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እውነት እላችኋለሁ፤ በሚመጣው አዲስ ዓለም የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን ላይ በሚቀመጥበት ጊዜ፣ እናንተም የተከተላችሁኝ በዐሥራ ሁለት ዙፋን ላይ ተቀምጣችሁ በዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ላይ ትፈርዳላችሁ።” አዲስ አለም የሚለውን ነው የኢንግሊዘኛው Regeneration የሚለው ነው ። 1954ቱ አዲስ አለም የሚለውን **በዳግመኛ ልደት** ነው የሚለው ። ሌላኛው ይህንን ቃል የምናገኘው በቲቶ መፅሐፍ ላይ ነው ። — ቲቶ 3፥5 (አዲሱ መ.ት) ። “ስላደረግነው የጽድቅ ሥራ ሳይሆን፣ ከምሕረቱ የተነሣ አዳነን። ያዳነንም ዳግም ልደት በሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ነው፤”

ይህንን ቃል በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩ ግሪካውያን ሲጠቀሙት ምን ነበር የሚያስቡት ? በእነርሱ አስተሳሰብ አለም Recycle ታደርጋለች ብለው ያስባሉ ። አስቀድሞ አለም Burn ታደርግና ከእዚያም Reborn ታደርጋለች ብለው ያስባሉ ። ይህንን ነው ፓሌንጄኔሲያ ብለው የሚጠሩት ። ከወደፊት ተስፋ ጋር እያይዘው ነው የሚጠቀሙት ። ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል ላይና ጳውሎስ በቲቶ መልዕክት ላይ ይህንን ቃል ሲጠቀሙ ምን አይነት መልዕክት እያስተላለፉ ነው ? ኢየሱስ በማቴ 19 ሲጠቀመው ሰፊውን አውድ በመያዝ አንድ ፣ ብቸኛና እውነተኛ ተስፋ አለ እርሱም ወደፊት ይሆናል የሚለውን እርግጠኛነት ሲሰጥ ፣ ጳውሎስ በቲቶ ላይ ደግሞ ይህ የወደፊቱ ተስፋ መጀመሪያ Renew የሆነ ነገር ይፈልጋል ማለትም ለአዲሱ ሰማይና ምድር አዲስ ልብ ያስፈልጋል እያለ ነው ።

**– Regeneration የሚመልሰው ጥያቄ ምንን ነው ?**

የዚህ አስተምህሮ ዋናው ትኩረት ለሚከተለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ነው ፦ አንዱ ሰው ለምን በወንጌልን ያምናል? ሌላው ደግሞ ለምን በወንጌል አያምንም ? ማለትም አንድ ሰው ብልህ ስለሆነ፣ የተሻለ የማመዛዘን ችሎታ ስላለው ነው የወንጌልን መልእክት አስፈላጊነት እንዲገነዘብ ያስቻለው ? ወይስ እግዚአብሔር በሚያድናቸው ሰዎች ሕይወት ውስጥ ልዩ የሆነ ነገር ሰላደረገ ነው? እነዚህን ጥያቄዎች ከመመለስ እንጀምር ።

**– ሰዎች ወንጌል ተሰብኮላቸው በክርስቶስ የማያምኑት ለምንድነው ?**

ይህ ከ Total depravity ጋር ይያያዛል ። የሰው ልጅ ሁለንተናው በኃጢአት ከመበከሉ ለእግዚአብሔር ነገር ሙት ከመሆኑ ጋር የተገናኘ ነው ።– ዮሐንስ 5 (አዲሱ መ.ት) ። ³⁶ “እኔ ግን ከዮሐንስ ምስክርነት የላቀ ምስክር

አለኝ፤ እንድፈጽመው አብ የሰጠኝ፣ እኔም የምሠራው ሥራ አብ እንደ ላከኝ ይመሰክራል። ³⁷ የላከኝ አብ ራሱ ስለ እኔ መሰክሮአል፤ እናንተም ከቶ ድምፁን አልሰማችሁም፤ መልኩንም አላያችሁም፤ ³⁸ የላከውንም ስላላመናችሁ ቃሉ በእናንተ አይኖርም። ³⁹ በእነርሱ የዘላለም ሕይወትን የምታገኙ እየመሰላችሁ፣ መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ፤ እነዚሁ መጻሕፍት ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፤ ⁴⁰ እናንተ ግን፣ ሕይወት እንዲኖራችሁ ወደ እኔ መምጣት አትፈልጉም። ⁴¹ "እኔ ከሰው ክብር አልቀበልም፤ ⁴² ነገር ግን እናንተን ዐውቃችኋለሁ፤ የእግዚአብሔርም ፍቅር በልባችሁ እንደሌለ ዐውቃለሁ። ኢየሱስ እዚህ ጋር ምን እያለ ነው ? በእኔ ልታምኑ ያልቻላችሁት ልባችሁ እኔን ስለሚጠላ ነው በማለት ችግሩ የውስጥ የልብ ችግር መሆኑን ይነግረናል ። ማለትም ሰዎች ወንጌልን የማይቀበሉት ልባቸው በጨለማ የተዋላ ስለሆነ ነው ማለት ።

– ሐዋርያት 7፥51 (አዲሱ መ.ት) ። "እናንት ልባችሁና ጆሮአችሁ ያልተገረዘ፣ አንገተ ደንዳኖች ልክ እንደ አባቶቻችሁ መንፈስ ቅዱስን ሁል ጊዜ ትቃወማላችሁ።" ።

እስጢፋኖስ እየሰበከ ያለውን ወንጌል እነዚህ አይሁዳውያን ለምንድነው የሚቃወሙት ?ልባቸው ላይ ችግር ሰላለ ነው ይለናል ። ማለትም ልባቸው ያልተገረዘ ስለሆነ ነው ።

– ዮሐንስ 8 (አዲሱ መ.ት) ። ⁴² ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እግዚአብሔር አባታችሁ ቢሆን ኖሮ፣ እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፣ በወደዳችሁኝ ነበር፤ እርሱ ላከኝ እንጂ በገዛ ራሴ አልመጣሁም። ⁴³ የምናገረውን ለምን አታስተውሉም? ምክንያቱም ቃሌን መስማት ስለማትችሉ ነው።

እዚህ ጋር ኢየሱስ ጥያቄ ይጠይቅና መልሱን እራሱ ይመልሳል ። ኢየሱስ እየተናገረ ያለውን የማያስተውሉት ቃሉን መስማት ስለማይችሉ ነው ። እዚህ ጋር ስለሚታየው የጆሮ ችግር እየተናገረ አይደለም ። ስለ ልባቸው ዶንቆሮነት እያወራ ነው ። ስለዚህ ሺ ጊዜ ለአይድ ሰው ወንጌል ብትነግረው የልቡ ሁኔታ ካልተለወጠ ወደ ወንጌሉ እውነት ሊመጣ አይችልም ። እንኳን እኛ ኢየሱስንም አልሰሙትም ።

**– ታድያ ሌሎችስ ወንጌል ተሰብኮላቸው እንዴት ነው ወንጌሉን መቀበል ያቻሉት?**

እዚህ ጋር Calling matter ያደርጋል ። ሁለት አይነት Calling አለ ። general calling እና effectual calling. – ማቴዎስ 22፥14 (አዲሱ መ.ት) ። "የተጠሩት ብዙዎች፣ የተመረጡት ግን ጥቂቶች ናቸውና።" general calling ሁሉም ሰው የሚሰማው የወንጌሉን ጥሪ የሚያመለክት ነው ። ውጤታማ ጥሪ ደግሞ ሰዎችን ወደ ድነት መሳብ ነው ።

Westminster Confession Chapter 10 - Of Effectual Calling ምዕራፍ 10 - **እግዚአብሔር አስቀድሞ ለሕይወት የወሰናቸው ሁሉ ፥ እነሱንም ብቻ ፣ እርሱ በወሰነውና ደስ ባለው ወቅት በልዩ ጥሪው ለመጥራት መልካም ፈቃዱ ሆነ ። ይህም ጥሪ በቃሉና በመንፈሱ መሳሪያነት ነው። በባሕርያቸ ከሚገኙበት ከኃጢአትና ከሞት በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ፀጋና ወደ ድነት ጠራቸው ። የእግዚአብሔርን ነገር እንዲገነዘቡ አእምሮአቸውን ለመንፈሳዊና ለድነት ነገሮች አበራላቸው ። የድንጋዩን ልብ ወሰዶ የሰጋን ልብ ሰጣቸው ። ፈቃዳቸውን በማደሰ ፥ በታላቅ ሀይሉ መልካሙን እንዲመርጡ አደረጋቸው ። በእርግጥም ወደጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አቀረባቸው። ይህንንም ሁሉ ሲያደርግላቸው ፥ ተገደው ሳይሆን በራሳቸው ምርጫ በፀጋው ፈቃደኛ እንዲሆኑ በማድረግ ነው ።**

ከእዚህ ጊር ተያይዞ ስፐርጅን እንዲህ ይላል፦ **"ሰው ያለ ፈቃዱ አልዳነም ፣ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ አሠራር ነው ፈቃደኛ የሆነውን ።**

መንፈስ ቅዱ ስራውን በመረጣቸው ሰዎች ውስጥ ስለሚሰራ ሰዎች የግድ ያምናሉ ለምሳሌ ሁለት አይነት ጥሪን እንመልከት ። የሰርግ ቤት ጥሪ ሲኖረን ከፈለግን እንሄዳለን ካልፈለግን እንቀራለን ። የፍርድቤት ጥሪ ከሆነ ግን ጥሪው በራሱ አንቀልቅሎ ነው የሚወስደው ። የእግዚአብሔርም ጥሪ ልክ እንደዚሁ ነው ። በእግዚአብሔር ከተጠራህ መቅረት አትችልም ። ይልቁኑም መምጣትህ አይቀርም ።

– ሐዋርያው ጴጥሮስ — 2ኛ ጴጥሮስ 1፥3 (አዲሱ መ.ት) ።"በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን እርሱን በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኀይል ሰጥቶናል።"

**"ተጠራ"** ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል (**καλέω) ካሌኦ** የሚል ሲሆን የሚያመለክተው ለኃጢአተኞች መዳን ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔርን ውጤታማ ጥሪ የሚያመለክት ነው ። **ካሌኦ** አንድ ኃጢአተኛ እንዲመጣ ከመጋበዝ ይልቅ ወደ እግዚአብሔር እየተሳበ ነው የሚለውን ሃሳብ ይይዛል። **— ሮሜ 1፥6 (አዲሱ መ.ት) ። "እናንተ ራሳችሁም ለኢየሱስ ክርስቶስ እንዲሆኑ ከተጠሩ መካከል ናችሁ።"** ውጤታማ ጥሪው በተለምዶ "የማይቋቋም ጸጋ" በመባል ይታወቃል

ብሉይ ኪዳን ላይም የሰዎች ትልቁ problem የልብ ጉዳይ ስለሆነ እግዚአብሔር ልብን ለመረወጥ promise ሲገባ እንመለከታለን ።

– ሕዝቅኤል 36 (አዲሱ መ.ት) [24] " 'ከአሕዛብ መካከል አሰወጣችኋለሁ፤ ከየአገሩ ሁሉ እሰበስባችኋለሁ፤ ወደ ገዛ ምድራችሁም መልሼ አመጣችኋለሁ። [25] ንጹሕ ውሃ እረጫችኋለሁ፤ እናንተም ንጹሕ ትሆናላችሁ፤ ከርኩሰታችሁ ሁሉና ከጣዖታቶቻችሁ ሁሉ አነጻችኋለሁ። [26] አዲስ ልብ እሰጣችኋለሁ፤ አዲስ መንፈስም በውስጣችሁ አሳድራለሁ፤ የድንጋይ ልባችሁን ከእናንተ አሰወግዳለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ።

እዚህ ጋር የሰዎችን ልብ በድንጋ ይመስለዋል ። በቃ ድንጋይ ሆኗል ምንም ያህል ጊዜ ቢለፈልፍ አይገባቸውም ። ስለዚህ ልባቸውን እለውጣለሁ እያለ ይመስላል ።

– ደግሞም በሐዋርያት ስራ ላይ ይህ promise ተግባራዊ በሆነ መንገድ የዋለ ይመስላል ።

– ሐዋርያት 16 (አዲሱ መ.ት) [14] ከሚያዳምጡትም ሴቶች መካከል ልድያ የምትባል አንዲት ሴት ነበረች፤ እርሷም እግዚአብሔርን የምታመልክና ከትያጥሮን ከተማ የመጣች የቀይ ሐር ነጋዴ ነበረች። ጌታም፣ ጳውሎስ የሚናገረውን በማስተዋል ትሰማ ዘንድ፣ ልቧን ከፈተላት። [15] እርሷና ቤተ ሰዎቿ ከተጠመቁ በኋላም፣ "በጌታ ማመኔን በርግጥ ከተረዳችሁልኝ ወደ ቤቴ መጥታችሁ ጥቂት ተቀመጡ" በማለት አጥብቃ ለመነችን።

ወንጌሉን ከሊድያ ጋር የሰሙ ሰዎች ነበሩ ነገርግን ወንጌሉን በልዩነት መቀበል ወይንም ማሰታዋል እንድትችል እግዚአብሔር ልቧን ሲከፍተው እንመለከታለን ። በእዚህም 1ኛ, የልብ መከፈት ለሰው ሁሉ እንዳልሆነና 2ኛ, ልብን የሚከፍት እራሱ እግዚአብሔር መሆኑን እንመለከታለን ።

– እንደዚሁም በተመሳሳይ መንገድ በቲቶ ላይ እናገኛለን ፦ ቲቶ 3 (አዲሱ መ.ት)[3] ቀደም ሲል እኛ ራሳችን ማሰተዋል የጐደለን፣ የማንታዘዝ፣ የተታለልን፣ ለተለያየ ምኞትና ምኞት ባሪያ ሆነን የተገዛን ነበርን፤ እየተጣላንና እርስ በርስ እየተጠላላን በክፋትና በምቀኝነት እንኖር ነበር። [4] ነገር ግን የአዳኛችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ፍቅር

በተገለጠ ጊዜ፣ [5] ስላደረግነው የጽድቅ ሥራ ሳይሆን፣ ከምሕረቱ የተነሣ አዳነን። ያዳነንም ዳግም ልደት በሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ነው፤

በእዚህ ምንባብ የነበርንበትን ሁኔታና የዳንበትን መንገድ ይገልፅልናል ። የነበርንበት ሁኔታ ማስተዋል የጎደለንና በተግባር ለእግዚአብሔር መታዘዝ የማንችል ሲሆን የዳንበት መንገድ ደግሞ በዳግም ልደት መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ነው ።

አንድን ግለሰብ ንሰሐ እንዲገባና ወንጌልን እንዲያምን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ብቻ እንጠቅሳለን። ማንም አስቀድሞ እግዚ አብሔር ካልሳበው በቀር ወደ ክርስቶስ ሊመጣ እንደማይችል በቅዱሳት መጻሕፍት እንመለከታለን። ሙሉ በሙሉ የተበላሸን በመሆናችን እግዚ አብሔርን በራሳችን አንመርጥም ። ስለዚህ ወደ ክርስቶስ የሚመጡት በመጀመሪያ በእሱ እንደሚሳቡ ግልጽ ነው ።

### – የ Regeneration ውጤቶች

አዲስ ልደት Repentance  እና Faithን ያመጣል ። በጠቅላላው አዲስ ሕይወትን ያመጣል ።

### 1ኛ, እግዚአብሔርን መውደድ እና ክፋትን መጥላት ይጀምራል ።

ይህንን በዮሐንስ ወንጌል ላይ መመልከት እንችላለን ። – ዮሐንስ 3 (አዲሱ መ.ት) ። [20] ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላል፤ አድራጎቱም እንዳይገለጥበት ወደ ብርሃን አይመጣም። [21] በእውነት የሚመላለስ ግን ሥራው በእግዚአብሔር የተሠራ መሆኑ በግልጽ ይታይ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል።”

ሰው ልቡ ከመለወጡ አስቀደ ብርሃንን የሚጠላ ደግሞ ጨለማን የሚወድ ነው ። ልቡ ሲለወጥ ግን የእዚያ ተቃራኒ ነው የሚሆነው ። ማለትም ጨለማን የሚጠላ ብርሃንን የሚወድ ነው የሚሆነው ። ልባቸው ያልተለወጡ ሰዎች ክፉ ስራቸው ሞት እንደሚያመጣባቸው እያወቁ ሞትን ይመርጣሉ እንጂ ክፋትን አይተውም ። አማኞች ግን ወደ ማስተዋል ስለመጡ የጨለማ ስራውች ውጤቱ ሞት እንደ ሆነ ስለሚያስተዉሉ ብቻ ሳይሆን ኃጢአት እግዚአብሔርን መበደል ስለሆነም ከክፋት ይርቃሉ ።

### 2ኛ , የጽድቅ ሰራዋችን እንድንሰራ ያደርገናል ።

— 1ኛ ዮሐንስ 2፥29 (አዲሱ መ.ት) “እርሱ ጻድቅ መሆኑን ካወቃችሁ፣ ጽድቅን የሚያደርግ ሁሉ ከእርሱ እንደ ተወለደ ታውቃላችሁ።”

### 3ኛ,  ህብረትን መውደድ እንጀምራለን ።

— 1ኛ ዮሐንስ 3፥14 (አዲሱ መ.ት) “ወንድሞቻችንን ስለምንወድ ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን፤ ፍቅር የሌለው ሁሉ በሞት ይኖራል።”

ከሞት ወደ ህይወት መሻገገራችን እንዱ ማረጋገጫው ወንድሞቻችንን  መውደዳችን ነው ። ሁሉም የታደሱ ሰዎች በክርስቶስ አንድ ስለሆኑ ፍቅር መለያቸው ነው።  ክርስቶስ እራሱ ይህንን ብሏል ።  — ዮሐንስ 13፥35 (አዲሱ መ.ት)  “እርስ በርሳችሁ ብት ዋደዱ፣ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ።””

# ንሰሃ እና እምነት

– ማርቆስ 1 (አዲሱ መ.ት) ። [14] ዮሐንስ እስር ቤት ከገባ በኋላ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ወንጌል እየሰበከ ወደ ገሊላ ሄደ፣ [15] "ጊዜው ደርሶአል፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች፤ ንስሓ ግቡ፤ በወንጌልም እመኑ" እያለ ይሰብክ ነበር።

በእዚህ ምንባብ የእግዚአብሔር መንግሰት አካል ለመሆን እምነት እና ንሰሃ አሰፈላጊ ነገሮች መሆናቸውን እንረዳለን ። እምነት እና ንሰሐ ለወንጌል እውነት  እጅግ አሰፈላጊ ምላሾች ናቸው ።  እምነት እና ንሰሐ የማይነጣጠሉ ድርጊቶች ቢሆኑም ሆኖም ግን የተለዩ ድርጊቶች ናቸው ። ምንድነው ንሰሐ ምንድነው እምነት ?

**– ንሰሃ**

ከንሰሐ ጋር በተያያዘ  በአዲስ ኪዳን ሦሰት ግሦች ጥቅም ላይ ውለዋል።

1ኛ, **μετανοέω (ሜታኖኦ)** የሚለው ቃል በቀጥታ ሲተረጎም በግሪኩ to change mind / to change your mind. አዕምሮን መቀየር ፣ አስተሳሰብን መለወጥ ።   – ሐዋርያት 3፥19 (አዲሱ መ.ት) ። "እንግዲህ ኀጢአታችሁ እንዲደመሰስ ንስሓ ግቡ፤ ከመንገዳችሁም ተመለሱ፤ ከጌታም ዘንድ የመታደስ ዘመን ይመጣላችኋል፤"

2ኛ,  (**μεταμέλλομαι**) (**መታሜሎማይ**) ይህ የጸጸትን ሃሳብ ያስተላልፋል።  በአዲስ ኪዳን ውስጥ በአንጻራዊ ሁኔታ በጣም አልፎ አልፎ ነው የሚከሰተው ። ማቴዎስ 21 (አዲሱ መ.ት) ። [28] ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "ምን ይመስላችኋል? ሁለት ወንዶች ልጆች ያሉት አንድ ሰው ነበረ፤ ወደ መጀመሪያው ልጁ ሄደ፣ 'ልጄ ሆይ፤ ዛሬ ወደ ወይኑ ቦታ ሄደህ ሥራ' አለው። [29] "ልጁም፣ 'አልሄድም' አለው፤ ኋላ ግን ተጸጽቶ ሄደ።

3ኛ, (**έπιστρέφω**) **ኢፒስቲሪፎ** ይህ ቃል የተገባር ለውጥን አፅንዖት ይሰጣል ። የተሰሎንቄ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ከመመለሳቸው ጋር ተያይዞ ይህ ቃል ተጠቅሳል ።   – 1ኛ ተሰሎንቄ 1፥9 (አዲሱ መ.ት) ። "በእንዴት ያለ አቀባበል እንደ ተቀበላችሁንና ሕያውና እውነተኛ የሆነውን አምላክ ለማገልገል ከጣዖታት ወደ እግዚአብሔር እንዴት እንደ ተመለሳችሁ እነርሱ ራሳቸው ይናገራሉ፤" ንሰሐ ማለት በአጭሩ  የአስተሳሰብ ለውጥ የሚያመጣው የአኗኗር ለውጥ ማለት ነው ። ወይንም የአስተሳሰብ ለውጥን ተከትሎ የሚመጣ የተገባር ለውጥ ማለት ነው ።

**– ሀሰተኛ ንሰሃ**

በስራነው ወይንም በድርጊቱ ማፈርና እና ማዘን ነገር ግን ባሉበት የተሳሳተ ድርጊት መቀጠል ንሰሃ አይደለም ። በጣም ብዙ ሰዎች ቤተክርስቲያን መጥተው የንሰሃ ፀሎት ሰለፀለዩ ንሰሃ የገቡ ይመስላቸዋል ። እውነተኛ ንሰሃ የንሰሃ ፀሎት ከመፀለይ ያልፋል ። ደግሞም ንሰሃችን ኃጢአታችንን እንድንጠላ ካላደረገ እውነተኛ ንሰሃ አይደለም ። እድሜ ልካችንን ኃጢአት እየሰራን ለውጠኝ ለውጠኝ ለውጠኝ ለውጠኝ ጌታ ሆይ የሚል መዝሙር ብንዘምር ዋጋ የለውም ። እውነተኛ የመፅሐፍ ቅዱስ ንሰሐ ከመፀፀት ወይንም ከመከፋት በላይ ነው ። in fact this is part of repentance. Repentance is not emotion. Repentance is decision.  የሀሰተኛ ንሰሃ ምሳሌ ይሁዳ መመልከት እንችላለን ፦ ማቴዎስ 27 (አዲሱ መ.ት) ።[3] አሳልፎ የሰጠው ይሁዳም ኢየሱስ እንደ ተፈረደበት ባየ ጊዜ ተጸጸተ፤ የወሰደውን ሠላሳ ጥሬ ብር ለካህናት አለቆችና ለሕዝቡ ሽማግሌዎች መልሶ በመስጠት፣ [4] "ንጹሕ ሰው አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ" አለ። እነርሱም፣ "ታዲያ እኛ ምን አገባን፤ የራስህ ጉዳይ ነው!" አሉት። [5] ስለዚህ ይሁዳ ብሩን በቤተ መቅደስ ውስጥ ወርውሮ ወጣ፤ ሄደም ራሱን ሰቅሎ ሞተ።

ነገር ግን ይህ የወንጌል ንሰሐ አልነበረም። ይልቁንም ተሰፋ መቁረጥ እና ራሰን ለሞት ያደረሰ ሀዘን ነበር።

ጳውሎሰ "ሞትን የሚያመጣ ሀዘን የዓለም ሀዘን" ብሎታል ። — 2ኛ ቆሮንቶሰ 7፥10 (አዲሱ መ.ት) ። "እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሐዘን ወደ ድነት ለሚያደርሰ ንሰሓ ያበቃል፤ ጸጸትም የለበትም። ዓለማዊ ሐዘን ግን ለሞት ያበቃል።"

**– እውነተኛ ንሰሃ**

ለእውነተኛ ንሰሃ ሁለት የመፅሐፍ ቅዱሰ ምንባባትን እንመልከት ። – ሉቃሰ 15 (አዲሱ መ.ት) ። [11] ደግሞም ኢየሱሰ እንዲህ አላቸው፤ "አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት። [12] ከእነርሱም ታናሹ ልጅ አባቱን፣ 'አባቴ ሆይ፤ ከሀብትህ ድርሻዬን ሰጠኝ' አለው፤ አባትየውም ሀብቱን ለልጆቹ አካፈላቸው። [13] "ብዙም ቀን ሳይቈይ፣ ታናሹ ልጅ ድርሻውን ሁሉ ጠቅልሎ ወደ ሩቅ አገር ሄደ፤ በዚያም በማጋጣነት ንብረቱን አባከነ። [14] እርሱም ያለውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ፣ በዚያ አገር ሁሉ ጽኑ ራብ ሆነ፤ ይቸገርም ጀመር። [15] ሰለዚህ ከዚያ አገር ነዋሪዎች አንዱን ተጠጋ፤ ሰውየውም ዐሣማ እንዲቀልብለት ወደ ዕርሻው ላከው። [16] ዐሣማዎቹ የሚመገቡትን ዐሠር እንኳ ለመብላት ይመኝ ነበር፤ ነገር ግን ይህን እንኳ የሚሰጠው ሰው አልነበረም። [17] "ልብ በገዛ ጊዜ ግን እንዲህ አለ፤ 'ሰንቱ የአባቴ ሠራተኛ ምግብ ተርፎታል፤ እኔ ግን እዚህ በራብ ልሞት ተቃርቤአለሁ [18] ተነሥቼ ወደ አባቴ ልሂድና፣ እንዲህ ልበለው፤ "አባቴ ሆይ፤ በሰማይና በአንተ ፊት በድያለሁ፤ [19] ከእንግዲህ ልጅህ ተብዬ ልጠራ አይገባኝም፤ ከተቀጠሩት አገልጋዮችህ እንደ አንዱ ቍጠረኝ።' [20] ሰለዚህም ተነሥቶ ወደ አባቱ ሄደ። "ነገር ግን፣ እርሱ ገና ሩቅ ሳለ፣ አባቱ አይቶት ራራለት፤ ወደ እርሱም እየሮጠ ሄዶ ዐቅፎ ሳመው።

ይህ ታናሽ ልጅ ያደረገውን ነገር እንመልከት አባቱን በደለው ፣ ደግሞም አባቱን መበደሉን በልቡ ተረዳ ፣ አባቱን ይቅርታ ለመጠየቅ ወሰነ ሄዶም ጠየቀው ። እነዚህ ድርጊቶቹ የንሰሃን ቅደም ተከት ያሟሉ ናቸው ።

በሁለተኛነት የ ዘኪዮሰን ታሪክ እንመልከት ። ዘኪዮሰ ንብረቱን ሁሉ በመሸጥ ፣ ገንዘቡን ለድሆች በመሰጠትና ከዚያም ኢየሱሰን በመከተል ይታወቃል። – ሉቃሰ 19 (አዲሱ መ.ት) ። [1] ኢየሱሰ ወደ ኢያሪኮ ገብቶ በዚያ አልፎ ይሄድ ነበር። [2] ሰሙ ዘኬዎሰ የተባለ አንድ ሰው በዚያ ነበረ፤ ዋና ቀረጥ ሰብሳቢና ሀብታም ነበረ። [3] እርሱም ኢየሱሰ የተባለው የትኛው እንደሆነ ሊያይ ይፈልግ ነበር፤ ቁመቱ አጭር ነበረና ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ሊያየው አልቻለም። [4] ኢየሱሰ በዚያ መንገድ ያልፍ ሰለ ነበርም፣ ሊያየው ወደ ፊት ሮጦ አንድ ሾላ ዛፍ ላይ ወጣ። [5] ኢየሱሰም እዚያ ቦታ ሲደርሰ፣ ቀና ብሎ፣ "ዘኬዎሰ ሆይ፤ ዛሬ አንተ ቤት መዋል ይገባኛልና ፈጥነህ ውረድ" አለው። [6] እርሱም ፈጥኖ ወርዶ በደሰታ ተቀበለው። [7] በዚያ የነበሩ ሰዎችም ይህንን አይተው፣ "ከኀጢአተኛ ቤት ገብቶ ሊሰተናገድ ነው።" በማለት ሁሉም ማጕረምረም ጀመሩ። [8] ዘኬዎሰ ግን ቆመና ጌታን፣ "ጌታ ሆይ፤ እነሆ ካለኝ ሀብት ሁሉ ግማሹን ለድኾች እሰጣለሁ፤ ማንንም በሐሰት ቀምቼ ከሆነ፣ አራት ዕጥፍ አድርጌ እመልሳለሁ" አለው። [9] ኢየሱሰም እንዲህ አለው፤ "ይህ ሰው ደግሞ የአብርሃም ልጅ ሰለ ሆነ፣ ዛሬ መዳን ወደዚህ ቤት መጥቶአል፤ [10] ምክንያቱም የሰው ልጅ የመጣው የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን ነው።"

በተለይም ንሰሃ በዕብራይሰጡ to the ground የሆነ ቃል ነው ። የቃሉም ትርጉም" turning around" በቀጥታ መዞር ፣ መንገድ መቀየር ማለት ነው ። ወደ ምሰራቅ ከነበርንበት ወደ ምዕራብ 180 ዲግሪ መዞር ነው ። ለእግዚአብሔር ጀርባ ሰጥተን ከነበረ ወደ ፊቱ 180 ዲግሪ መዞር ነው ። ንሰሐ ያለፈን ሰህተት እንደሆነ ማወቅ እና ወደፊት በትክክል ለማሰብ መወሰንን ያካትታል ። ንሰሐ የገባ ሰው ቀደም ሲል ሰለተቀበለው አሰተሳሰብ ሁለተኛ (ተለዋጭ ) ሀሳብ አለው ። ሰለ እግዚአብሔር ፣ ሰለ ሀጥያት ፣ ሰለ ቅድሰና እና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ የአመለካከት ለውጥ ፣ አዲሰ የአሰተሳሰብ መንገድ አለው ።በአጭሩ ንሰሐን ለመረዳት ኃጢአትን መረዳት ወሳኝ ነው ። ኃጢያት ማለት missing the mark ማለት ሲሆን - Repentance

ደግሞ ወደ ትክክለኛው መንገድ መመለስ ነው ።

**– ንሰሐ የእግዚአብሔር ነፃ ሰጦታ ነው**

ሰዎች በራሳቸው ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ ካሉበት ክፉ መንገድ ልመለስ ብለው መመለስ አይችሉም ። እንደውም በተቃራኒው ክፋታቸው እና አመፃቸው በእየለቱ እየጨመረ ይሄዳል ። ነገርግን ከክፉ ድርጊታቸው መመለስ የሚችሉት የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት ሲኖረው ብቻ ነው ። – ሐዋርያት 5፥31 (አዲሱ መ.ት) ። "እርሱም ለእስራኤል ንስሓንና የኀጢአትን ስርየት ይሰጥ ዘንድ፣ እግዚአብሔር የሁሉ ራስና አዳኝ አድርጎ በቀኙ ከፍ ከፍ አደረገው።" እዚህ ጋር ከንሰሃ ጋር ጎን ለጎን የቀረበውን መመልከት ንሰሃ ሰጦታ መሆኑን እንድንረዳ ያደርጋል ። ይህም የኃጢአት ሰርየት ነው ። የኃጢአትን ሰርየት ከእግዚአብሔር ውጪ ሊሰጥ የሚችል እንደሌለ ሁሉ ንሰሃም ከእግዚአብሔር ውጪ ሊሰጥ የሚችል የለም ።

– ሐዋርያት 11፥18 (አዲሱ መ.ት) ። "ይህን በሰሙ ጊዜም የሚሉትን አጥተው እንዲህ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ "ይህማ ከሆነ፣ አሕዛብም ወደ ሕይወት ይመጡ ዘንድ፣ እግዚአብሔር ንስሓን ሰጥቷቸዋል ማለት ነዋ።"" በእነዚህ ሁለቱ የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባባት በግልጽ እንደምንመለከተው ንሰሃ የእግዚአብሔር ሰጦታ ነው ። ይህንን ሰጦታ ማንም ያልተቀበለ ሰው ከክፋት ድርጊቱ መመለስ አይችልም ።

**– እምነት**

እምነት ማለት "Saving Faith" የሚያድን እምነት ማለት ነው ። ብዙ ሰው ከ Saving faith ውጪ ያለውን faith አምኖ እንደሚድን ያስባል ። አንድ ፈላሰፋ እንዳለው እግዚአብሔር የለም ብዬ ከሚኖር አለ ብዬ ባይኖር ይሻላል ይላል ። ይህ ጥሩ አገላለጽ ነው ። እግዚአብሔር የለም ከማለትም በጣም የተሻለ ነው ። ነገር ግን ይህንን ማመን ብቻውን አያድንም ። እርሱ ብቻ አይደለም ሰው እግዚአብሔር አለ ከሚለው እምነት ተሻግሮ እግዚአብሔር ይፈውሳል ተአምራትን ያደርጋል ብሎ ቢያምንም ይህ እምነቱ አያድነውም ። ነገር ግን የሚያድነው እምነት ሙሉ በሙሉ መፅሐፍ ቅዱሰን ማመንና በድነት ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር ለማዳን የመረጠው መንገድ ኢየሱስ ክርሰቶሰ ብቻ መሆኑን ማመን ነው ።

**Saving Faith ሶሰት ነገሮችን ያካትታል ።**

**Notitia, Assensus, and Fiducia ( ኖቲቲአ ፣ አሰንሱሰ እና ፊኢዱሲአ)** እነዚህ ሶሰቱ የላቲን ቃላት ናቸው ። knowledge, assent and trust.(እውቀት ፣ ሰምምነት እና መደገፍ) እነዚህ ነገሮች ሙሉ በሙሉ የክርሰቶሰ ማንነት እና ሰራ ላይ የሚያርፉ ናቸው ።

**ጆን ካልቪን እንደሚለው ፦ እምነት ልክ እንደ 'ባዶ የአበባ ማሰቀመጫ' በክርሰቶሰ ጽድቅ የተሞላ የእማኝ በእግዚአብሔር ፊት የመቆምና የዘላለም ሕይወት ርሰት የሚሆንበት ብቸኛ መሠረት ነው።**

j.i. packer. Faith is "an appropriating instrument, an empty hand outstretched to receive the free gift of God's righteousness in Christ." ጄ አይ ፓከር እንደዚህ ይላሉ ፦እምነት "የእግዚአብሔርን የጽድቅ ሰጦታ በክርሰቶሰ ለመቀበል የተዘረጋ ባዶ እጅ" ነው።

አንድ አንድ አሰተማሪዎች እምነትን ለመዳን ከሰው እንደሚጠበቅበት እንደ አዲሰ ህግ ይመለከቱታል ። ጆን ኦወን እምነትን በተመለከተ ሰዎች የሚጸድቁበት እንደ አዲሰ ህግ አድርጎ የሚያሰበውን **የሪቻርድ ባክተርን** የተሳሳቱ አመለካከቶችን በይፋ አውግዟል።

**– እምነት የእግዚአብሔር ነፃ ስጦታ ነው**

— ፊልጵስዩስ 1፥29 (አዲሱ መ.ት) ። “በክርስቶስ እንድታምኑ ብቻ ሳይሆን ስለ እርሱ መከራ እንድትቀበሉም ይህ ጸጋ ተሰጥቶአችኋልና፤”

— 2ኛ ጴጥሮስ 1፥1 (አዲሱ መ.ት) ። “የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና ሐዋርያ ስምዖን ጴጥሮስ፤ በአምላካችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ በኩል እንደ ተቀበልነው ዐይነት ክቡር እምነት ለተቀበሉት፤” ተቀበሉ የመለው ቃል እኛ ጋር የሌለ ሌላ አካል ጋር ያለን ነገር የሚገልጽ ቃል ነው ።

**– እምነት ለምን ሰጦታ ሆነ ?**

የሰው ልጆች ማመን ስለማይችሉ ። **— ዮሐንስ 3፥32 (አዲሱ መ.ት)። “ያየውንና የሰማውን ይመሰክራል፤ ነገር ግን ምስክርነቱን ማንም አይቀበልም፤”** እምነትን በጣም ብዙ ሰዎች ቀላል አድርገው ሲናገሩ አሰተውያለሁ ። እመን ብቻ ብለው ሰዎች ማመን እንደሚችሉ አድርገው የሚያሰቡ ብዙ ሰዎች አሉ ። ነገር ግን ማመን እንደሚታሰበው ቀላል ነገር አይደለም ።

**– ለምንድነው ማመን ያልቻሉት?**

በሁለት ምክንያት ፦ 1ኛ, totally depraved ስለሆንን ። – ዮሐንስ 8 (አዲሱ መ.ት) ። [42] ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እግዚአብሔር አባታችሁ ቢሆን ኖሮ፣ እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፣ በወደዳችሁኝ ነበር፤ እርሱ ላከኝ እንጂ በገዛ ራሴ አልመጣሁም። [43] የምናገረውን ለምን አታስተውሉም? ምክንያቱም ቃሌን መስማት ስለማትችሉ ነው።

2ኛ, የእግዚአብሔር እውነት ከሰዎች መረዳት በላይ ስለሆነ ። — 1ኛ ቆሮንቶስ 2፥14 (አዲሱ መ.ት) ። “መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው ከእግዚአብሔር መንፈስ የሆነውን ነገር ሊቀበል አይችልም፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለው ነገር ለእርሱ ሞኝነት ነው፤ በመንፈስም የሚመረመር ሰለ ሆነ፣ ሊረዳው አይችልም።”

ንሰሐ መግባት ፦ ከኃጢአት መራቅና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር መዞር ሲሆን

እምነት ፦ የኢየሱስ ክርስቶስን ፅድቅ መቀበል እና የእኛን ድካምና ኃጢአት ለእርሱ መሰጠት ነው ።

እምነትና ንስሃ በተመሳሳይ ጊዜ ይከሰታሉ ። ነገርግን ቅደም ተከተሉ ላይ ግን የተለያዩ ምልከታዎች አሉ ። ነገር ግን የተሻለው መንገድ እምነት አመክንዮአዊ በሆነ መልኩ ከንሰሃ ይቀድማል የሚለው ነው ። ንሰሐ መግባት የእምነት ውጤት ነው ። ግን ይህ ድምዳሜ የግድ አይደለም ። ያመኑት ንሰሐ ይገባሉ፣ ንሰሐ የገቡ ደግሞ ያምናሉ። ንሰሐ የእምነት ፍሬ ነውና ለመዳን መሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ አይደለም ።

# Justification

**– ፅድቅ ምንድነው ?**

Justification እና Righteousness ትንሽ ለየት ያለ ትኩረት አላቸው። አማርኛው ሁለቱንም አንድ አድርጎ ነው የሚገልፀው ። **Justification** "ጽድቅን መቁጠር" ወይም " ጻድቅ መባል " ወይንነ ህጋዊ አዋጅ ነው ። በጳውሎስ መልእክቶች የጽድቅ ትኩረት ባብዛኛው ከእዚህ ጋር የተያያዘ ነው ። Righteousness ግን በአብዛኛው የሚያገለግለው virtuous character በጎነትን ወይን በጎ ስነምግባርን ወይንም የክርስቲያን Virtue ለማመልከት የሚውል ቃል ነው። ይህ ፅድቅ ፍፁም የሆነ የሞራል እና የተግባር ንፅህና ነው ። ስለ ፅድቅ ስናስብ በፍጥነት አእምሮአችን ላይ የሚመጣው እግዚአብሔር ነው ። - ፅድቅ የእግዚአብሔር ባህሪ ነው ፣ ፅድቅ የእግዚአብሔር ገቢር ነው ።

**– ሰዎች ይህ ባህሪ እና ገቢር አላቸው ?**

ሰዎች ይህ አይነቱ ባህሪ ሆነ ገቢር የላቸውም ። ምክንያቱም ሰዎች ኃጢአተኞች ስለሆኑ ። ታድያ በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር የተለየ ምስኪን ሰው እንዴት ነው ወደ እግዚአብሔር የሚቀርበው ?

ይህን ጥያቄ እዮብ ይጠይቃል ። — ኢዮብ 9፥2 (አዲሱ መ.ት) ። "" ነገር ግን ሥጋ ለባሽ በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ጻድቅ ሊሆን ይችላል?" የዚህን ጥያቄ ጥልቀት እንመልከት ። 1ኛ, እንደሚታወቀው ኢዮብ ከክፋት የራቀ ፣ ቅን ፣ እግዚአብሔርን የሚፈራ እርሱን ላለመበደል የሚጠነቀቅ ሰው ነው ። ይህ ሰው ስጋ ለባሽ በእግዚአብሔር ፊት እንዴት መቆም ይችላል ማለቱ በእግዚአብሔር ፊት መቆም እጅግ አሳሳቢ እና ፍፁም የሆነ ንፅህናን የሚጠይቅ መሆኑን እንድንረዳ የሚጋብዝ ነው ። 2ኛ, የኢዮብ መፅሐፍ ከዘፍጥረት መፅሐፍ ቀድሞ የተፃፈ የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያ መፅሐፍ ነው ተብሎ ይታሰባል ። ይህ ምንን ያሳየናል - የመጀመሪያዎቹ ሰዎች እንኳን ትኩረታቸው ሰው እንዴት በፃድቁ እግዚአብሔር ፊት መቅረብ ፣ መቆም ይችላል የሚል ነው ።

**– ፅድቅ ይህን ያህል ለምን አስፈላጊ ሆነ ?**

— ማቴዎስ 5፥6 (አዲሱ መ.ት) ። "ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፤ ይጠግባሉና።" ይህ ከተፈጥሮ ስርአት ጋር የተያያዘ ነው ። ምግብ ለሰዎ ልጆች ህይወት አስፈላጊ እንደሆነ እና የሰው ልጅ ህይወት ቀጣይነቱ በምግብ ላይ እንደሚመሰረት ሁሉ ፅድቅም ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖረን ህብረት እና ለሚኖረን ቀጣይነት መሰረታዊ ነገር ነው ።

— ማቴዎስ 6፥33 (አዲሱ መ.ት) ። "ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፤ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል።" በእዚህኛው ክፍልም ከሁሉም ነገር መቅደም ያለበት የእግዚአብሔር መንግሰት ጉዳይ ወይንም ፅድቅ ነው ። ከሁሉምን ነገር ቅድሚያ የሚፈለግ ነገር ያ እጅግ አስፈላጊ ነገር ቢሆን ነው ።

በእዚህ አጋጣሚ ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል ሳይሆን እነዚህ ሁሉ ይጨመርላችኋል ነው የሚለው ። እነዚህ ሁሉ የሚለው የትኞቹን ነው ? – ማቴዎስ 6 (አዲሱ መ.ት) ። 25 "ስለዚህ እላችኋለሁ፣ ስለ ኑሮአችሁ ምን እንበላለን? ምን እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? በማለት አትጨነቁ። ሕይወት ከምግብ፣ ሰውነትስ ከልብስ አይበልጥምን? 26 እስቲ የሰማይ ወፎችን ተመልከቱ፤ አይዘሩም፤ አያጭዱም፤ በጐተራም አያከማቹም፤ ይሁን እንጂ የሰማዩ አባታችሁ ይመግባቸዋል። እናንተ ከእነርሱ እጅግ አትበልጡምን? 27 ለመሆኑ ከእናንተ መካከል ተጨንቆ በዕድሜው ላይ አንዲት ሰዓት መጨመር የሚችል አለን? 28 "ደግሞስ ስለ ልብስ ለምን

ትጨነቃላችሁ? እስቲ የሜዳ አበቦችን ተመልከቱ፤ አይለፉም፤ ወይም አይፈትሉም። [29] ስለዚህ እላችኋለሁ፤
ያን ያህል ክብር የነበረው ንጉሥ ሰሎሞን እንኳ ከእነዚህ አበቦች እንደ አንዲቱ አልለበሰም። [30] እናንተ እምነት
የጐደላችሁ እግዚአብሔር ዛሬ ታይቶ በነጋታው እሳት ውስጥ የሚጣለውን የሜዳ ሣር ይህን ያህል ካለበሰ
እናንተንማ እንዴት አብልጦ አያለብሳችሁ? [31] ስለዚህ፣ ‘ምን እንበላለን? ምን እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን?’
ብላችሁ አትጨነቁ፤ [32] አሕዛብ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለማግኘት ይጨነቃሉና፤ የሰማዩ አባታችሁም እነዚህ ሁሉ
ለእናንተ እንደሚያ ሰፈልጓችሁ ያውቃል። [33] ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን
እሹ፤ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል።

እነዚህም ሁሉ የተባሉት መብል ፣ መጠጥ እና ልብስ እንጂ ሌሎች ነገሮችን በሙሉ እግዚአብሔር ቃል አልገባልንም ። እነዚህ ነገሮች ግን ለመኖር መሰረታዊ ነገሮች ናቸው ።በሌላ አገላለጽ ከምትበሉትም ፣ ከምትለብሱትም ለመኖር መሰረታዊ ከሆኑትም ነገሮች በላይ የእግዚአብሔርን መንግሰት እና ፅድቅ ፈልጉ እያለ ነው ። ፅድቅ ያን ያህል አስፈላጊ ነገር ነው ።

– **What is Justification ?** Justify በ Greek (δίκαιος) ዲካዮ ማለት ሲሆን (to declare righteous) ይህ የፍርድ ቤት ቋንቋ ነው ። መጽሃፍ ቅዱሳዊው የጽድቅ አስተምህሮ የእግዚአብሔር “ድርጊት” ነው ። የህጋዊ መግለጫ፣ የፍርድ አዋጅ ነው ። የፍርድ ቀን የመለኮታዊው ዳኛ ፍርድ ነው።

1ኛ, ከቁጣ ወደ ሰርየት- የቤተ መቅደስ አገላለጽ ነው ።

2ኛ, ከባርነት ወደ ነፃነት- የ slave market. የንግድ አገላለጽ ነው ።

3ኛ, ከኃጢአት በደል ወደ ፅድቅ- የፍርድ ቤት አገላለጽ ነው ።

4ኛ, ከጥል ወደ እርቅ - የቤተሰብ አገላለጽ ነው ።

ይህ ፅድቅ ጊዜያዊ ማስታወቂያ ሳይሆን ፣ የማይሻር ወይም እስከ መጨረሻው ቋሚ የሆነ የአንድ ጊዜ አዋጅ ነው። የፅድቃችንም ሁኔታ ተለዋዋጭ አይደለም ። ፅድቅ የሚቀንስም የሚጨምርም ሁኔታ አይደለም ። እግዚአብሔር ሰውን የሚያፀድቀው አንድ ጊዜ እና ለዘለዓለም ነው ። የሚደጋገም ተግባር አይደለም ። ሰው ፀድቋል ወይም አልፀደቀም ። አማካይ ደረጃ የለውም ።

**– የፍርድ ቤት term ወይንም የዳኛው አዋጅ መሆኑን ከመፅሐፍ ቅዱስ እንመልከት**

በእዚህ ጉዳይ ላይ በርካታ የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባቦችን እንደ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል ። ለጊዜው አሁን በሚቀርቡት የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ላይ ብቻ ትኩረት እናድርግ ። — ዘዳግም 25፥1“በሰዎች መካከል ጠብ ቢሆን፥ ወደ ፍርድም ቢመጡ፥ ፈራጆችም ቢፈርዱባቸው፥ ጻድቁን፦ ደኅና ነህ፥ የበደለውንም፦ በደለኛ ነህ ይበሉአቸው።”

ዳዊትም በህግ ፊት ፃድቅ አለመሆኑን ባወቀ ጊዜ ልመናን ሲያቀርብ እናያለን። **– መዝሙር 143፥2 (አ. መ.ት.) ። “ሰው ሆኖ በፊትህ ጻድቅ የለምና፣ ባሪያህን ወደ ፍርድ አታቅርበው።”** ይህ ደግሞ እጅግ ግልጽ ያደርገዋል ።

በተጨማሪም በአዲስ ኪዳን ጳውሎስ ፅድቅን በሮሜ መፅሐፍ የህግ Term አድርጎ ይጠቅመዋል ። — ሮሜ 5፥16 (አዲሱ መ.ት) ። “ደግሞም የእግዚአብሔር ስጦታ እንደ አንዱ ሰው የኀጢአት ውጤት አይደለም፤ ምክንያቱም ፍርዱ የአንድን ሰው ኀጢአት ተከትሎ ኵነኔን አመጣ፤ ስጦታው ግን አያሌ መተላለፍን ተከትሎ ጽድቅን አመጣ።” ፍርድ ኩነኔ እና ፅድቅ በአንድነት ተያይዘው ነው የቀረቡት ።

– ሮሜ 8 (አዲሱ መ.ት) ።[33] እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚከስ ማን ነው? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፤ [34] ታዲያ የሚኰንን ማን ነው? የሞተው፣ እንዲሁም ከሞት የተነሣው፣ በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ ኢየሱስ፣ ስለ እኛ ይማልዳል። እዚህ ጋርም በተመሳሳይ መንገድ ክስ ፣ ኩነኔ እና ፅድቅ በአንድነት ተቀምጠዋል ስለዚህ በማያሻማ ሁኔታ የፍርድ ቤት አገላለጽ ነው ።

አፀደቀ የሚለው ቃል ህጋዊ አዋጅ ነው ። ህይወቱን በመለወጥ መልካም ያደርገዋል ማለት ሳይሆን ኃጢአተኛውን ፃድቅ ነህ በማለት በስልጣን ቃል ተናግሯል ማለት ነው ። በአንድ ሰው ላይ መፍረድ ያ ሰው በደለኛ መሆኑን ማወጅ ነው ። አንድ ሰውን በደለኛ አይደለም ብሎ ማወጅ ደግሞ ፃድቅ ነህ ብሎ ማወጅ ነው ።

**– የሰው ሁኔታ በፃድቁ በእግዚአብሔር ፊት ምን ይመስላል ?**

አንድም ፃድቅ ሰው የለም ። — ኢሳይያስ 64፥6 (አዲሱ መ.ት) ። "ሁላችን እንደ ረከሰ ሰው ሆነናል፤ የጽድቅ ሥራችን እንደ መርገም ጨርቅ ነው፤ ሁላችን እንደ ቅጠል ረግፈናል፤ ኀጢአታችንም እንደ ነፋስ ጠራርጎናል።"

— ኢዮብ 9፥2 (አዲሱ መ.ት) ። " ነገር ግን ሥጋ ለባሽ በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ጻድቅ ሊሆን ይችላል?"

— ሮሜ 3፥10 (አዲሱ መ.ት) ። "እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤ "ጻድቅ ማንም የለም፤ አንድም እንኳ፤"

ሰው ፃድቅ አለመሆን ብቻ ላይ ማቆም ተገቢ አይደለም ። ሰው እግዚአብሔርን በሀሳቡ በንግግሩና በድርጊቱ እግዚአብሔርን በድሏል ። ደግሞም ፍርድ ይጠብቀዋል ። – ሮሜ 14 (አዲሱ መ.ት) ። [10] ታዲያ አንተ በወንድምህ ላይ ለምን ትፈርዳለህ? ለምንስ ወንድምህን ትንቃለህ? ሁላችንም በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለንና፤ [11] እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፤ " 'እኔ ሕያው ነኝና'፤ 'ጕልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፤ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር ይመሰክራል' " ይላል ጌታ። [12] ስለዚህ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን።

**– ታዲያ እንዴት ነው ልንፀድቅ የምንችለው ?**

በራሱ በእግዚአብሔር ብቻ!

— 1ኛ ሳሙኤል 2፥25 (አዲሱ መ.ት) ። "አንድ ሰው ሌላውን ቢበድል፣ እግዚአብሔር ጣልቃ ገብቶ ይፈርዳል፤ ነገር ግን ሰው እግዚአብሔርን ቢበድል፣ ማን ይማልድለታል?" ከእግዚአብሔር በስተቀር ለሰው የሚደርስለት አካል የለም ። — ሮሜ 8፥33 (አዲሱ መ.ት) ። "እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚከስ ማን ነው? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፤" ማፅደቅ የእግዚአብሔር Act ነው ። ፍርድ ቤት ሄዶ አንድ ወንጀለኛ እራሱን በራሱ ወንጀለኛ አይደለሁም ነፃ ወጥቻለሁ ሊል አይችልም ። ነፃ ነው ሊለው የሚችለው ዳኛው ብቻ ነው ።

– ሮሜ 3 (አዲሱ መ.ት) [21] አሁን ግን ሕግና ነቢያት የመሰከሩለት፣ ከሕግ ውጭ የሆነ፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአል። [22] ይህ የእግዚአብሔር ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የሚገኝ ጽድቅ ነው። ልዩነት የለም፤ [23] ምክንያቱም ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል፤ [24] በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት እንዲያው በጸጋው ጸድቀዋል፤ [25] በደሙም በሆነው እምነት፣ እግዚአብሔር የማስተሰረያ መሥዋዕት አድርጎ አቅርቦታል፤ ይህንም ያደረገው ቀድሞ የተፈጸመውን ኀጢአት ሳይቀጣ በትዕግሥት በማለፍ ጽድቁን ለማሳየት ነው፤ [26] በአሁኑ ዘመን ይህን ያደረገው፣ ጽድቁን ይኸውም እርሱ ራሱ ጻድቅ ሆኖ፣ በኢየሱስ የሚያምነውን የሚያጸድቅ መሆኑን፣ ለማሳየት ነው።

ካልቪን መጽደቅ ሁለት ክፍሎችን ያቀፈ ነው ይላል Institutions በሚለው መፅሐፍ ላይ ። 1ኛ, "የኃጢአት ሰርየት ሲሆን ፦ ይህ ማለት፦ ኃጢአት በአማኙ መዝገብ ላይ አይቆጠርም ማለት ነው ። 2ኛ, የክርስቶስ ጽድቅ መቆጠር" በሁለተኛ ደረጃ፣ ጽድቅ በአማኙ ሂሳብ ላይ ይመዘገባል።

ይህንን በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛለን ። – ሮሜ 4 (አዲሱ መ.ት) ።[4] አንድ ሰው ሥራ ከሠራ ደመወዙ እንደ ስጦታ ሳይሆን እንደ ተገቢ ዋጋው ይቈጠርለታል። [5] ነገር ግን ለማይሠራው፣ ኃጥኡን ሰው ጻድቅ በሚያደርግ በእግዚአብሔር ለሚያምን ሰው፣ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል። [6] ዳዊትም ጽድቅ ያለ ሥራ ስለሚቈጠርለት ሰው ብፅዕና እንዲህ ብሎአል፤ [7] "መተላለፋቸው ይቅር የተባለላቸው፣ ኀጢአታቸው የተሰረየላቸው፣ ብፁዓን ናቸው። [8] ኀጢአቱን፣ ጌታ ከቶ የማይቈጥርበት ሰው ብፁዕ ነው።" ኃጢአቱ የማይቆጠርለት ደግሞም የራሱ ያልሆነ ፅድቅ የተቆጠረለት ኃጢአተኛ ነው ። Luther called it "an alien righteousness" ምፅአተኛ ፅድቅ

– የፅድቅ ምንጭ የእግዚአብሔር ፀጋ ነው ። ሮሜ 3:25-26

– የፅድቅ መገኛ የክርስቶስ መታዘዝ ነው ። ሮሜ 5:18-19

– የፅድቅ መንገድ እምነት ነው ።ሮሜ 3:28 - 5:1-2።

**– ከ Justification ጋር ተያይዞ የተነሱ የስህተት አመለካከቶች**

1ኛ, የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ምልከታ (በInfusion) ወይንም ሂደታዊ ነው ቅፅፈታዊ አይደለም ።

የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን መፅደቅ ከመቀደስ በኃላ የሚመጣው ነው ትላለች ። እምነት እና ሌሎች ኃይማኖታዊ ስርአቶችን በመፈፀም በእግዚአብሔር ፊት መቆም እና ቆሞ መቀጠል እንችላለን ትላለች ። የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን እምነት ለመፅደቅ መስፈርት ቢሆንም ብቻውን ግን በቂ እና የመጨረሻ መስፈርት አይደለም ብላ ታስተምራለች ። እምነት ብቻውን ለመፅደቅ አስፈላጊ ካልሆ ተጨማሪ መስፈርቶችን መፈፀም ያስፈልገናል ፣ ያለእነዛ ተጨማሪ መስፈርቶች ህይወት አናገኝም ብላ ታስተምራለች ። እምነት እና ስራዎች እንዲሁም ሌሎች ቅዱሳን መጨመር አለባቸው ብላ ታስተምራለች ። መጽደቅ፣ ለካቶሊክ፣ እግዚአብሔር ያለማቋረጥ በሰው ላይ የሚያደርገውን ድርጊት ይመለከታል።

2ኛ, NPP

የ NPP ትልቁ ጥያቄ ለመመለስ የሚሞክሩት What was 1st Century Judaism? ይሄ Historical question ነው ።

E.P Sandersበ 1977 ዓም Paul and Palestinian Judaism የሚል ፅሁፍ ፃፈ ። በጣም ብዙ ተቺዎች እንደሚሉት መፅሐፍ መባል ያለበት Paul and Palestinian Judaism ሳይሆን Palestinian Judaism and Paul ነው መባል ያለበት ምክንያቱም 80% የሚዳሰሰው Palestinian Judaismን ነው ይላሉ ።

በዋናነት ለመመለሰም የሚሞክረው ጥያቄ **What were the requirements for get in to the covenant ? and stay in the covenant.** እንዴት ነው ወደ ኪዳኑ መግባት የሚቻለው? እናም ደግሞ እንዴት ነው ኪዳኑ ውስጥ መቆየት የሚቻለው ? ለእዚህ ጥያቄ መልሱ Covenantal nomism ብሎ ይጠራዋል ። **በአጭሩ የ Covenantal nomism ሀሳብ you get in By God Election. By Grace. You stay in by keeping the commandments of God.**

ከእዚያ በመቀጠል James Dun በ 1982 The New perspective on Paul የሚልን ፅሁፍ ፃፈ ። በ Dun አስተሳሰብ Justification By Faith alon የጳውሎስ Central ሀሳቡ አይደለም ይላል ። በጳውሎስ መልዕክታት ውስጥ የገላትያ እና የሮሜ መልዕክት ውስጥ ብቻ ነው ። ሁለቱ መልዕክታት ውስጥም የተጠቀሰው በአይሁድ እና በአህዛብ መካከል የነበረውን ልዩነት ፈትቶ አንድ ስለማድረግ እንጂ የጳውሎስ ዋና ትኩረቱ Justification by Faith alone አይደለም ። **በእዚህም Vertical የሆነውን የፅድቅ ትርጉም ቀይሮት Horizontal አድርጎታል ። ማለትም Justification ኃጢአተኛው ሰው እንዴት በእግዚአብሔር ፊት ይቀርባል ሳይሆን አህዛብ ከአይሁድ ጋር እንዴት የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ይሆናሉ የሚለውን ነው የሚመልሰው ይላል ።**

ከእርሱ በኋላ ደግሞ NT Wright መጥቶ የሚመሳሰል ነገር አስተማረ ።

Wright, what saint Paul really said, page 75 ላይ.....**What Paul means by Justification, in this Context, Should be Clear. It is not "How you Became a Christian," So much as "how can tell who is the member of the covenant family."**

Wright ጽድቅን በነገረ ቤተ-ክርስቲያን ጎራ ያስቀምጣል። ፅድቅ ecclesiology እንጂ soteriology አይደለም ይላል ። ይህ የመጀመሪያው Justification ነው ይላል Further Justification የሚለው ደግሞ ከለ ። በሰዎች ስራ ላይ ተመስርቶ እግዚአብሔር ያፀድቃቸውል ይላል ።

እነዚህ ምልከታዎች ከላይ ከሰጠነው መፅሐፍ ቅዱሳዊ ትንተና አንፃር ስህተት ናቸው ።

**– ለምን በዕምነት ብቻ ማለታችን አስፈላጊ ሆነ?**

**ምክኒያቱም እውነተኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወንጌል ከሐሰት ወንጌሎች የምንለይበት እንዱ መለያ ባህሪ ስለሆነ ! በዕምነት ብቻን መካድ ወይንም በዕምነት ብቻ የሚለውን ትርጉሙን መቀየር አደጋ ላይ ያለው ወንጌል መያዝን የሚያሳይ ነው ። በእምነት ብቻ የሚለው ትምህርት በፕሮቴስታንቶች እና በካቶሊኮች መካከል ያለ ልዩነት ብቻ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ክርስትና እና በሁሉም ሃይማኖቶች እንዲሁም ትምህርቶች መካከል ያለው ልዩነት ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊው ክርስትና ከየትኛውም ሀይማኖቶች የሚለየው እግዚአብሔር በክርስቶስ የጨረሰው ስራ ባከናወነው ነገር ላይ ያተኮረ ሲሆን ሁሉም ሌሎች ሃይማኖቶች ግን በሰዎች ስራ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። በእምነት የመጽደቅን ትምህርትን ከተውን፣ ብቸኛውን የመዳን መንገድ እንተወዋለን። የራሳቸውን ፅድቅ ለመመሰረት የሚሞክሩ ወይም እምነትን ከሰራ ጋር የሚደባለቁ ሁሉ የእግዚአብሔርን ፍፁም የመመዘኛ ደረጃን መውጣት ይጠበቅባቸዋል ። Sola fideን የሚክዱ ሊያድናቸው የሚችለውን ብቸኛ ወንጌል አይቀበሉም እናም በግድ የሐሰት ወንጌልን ይቀበላሉ።**

## Doctrine Of Adoption / ልጅነት

Adoption Justificationንን ተከትሎ የሚመጣ ነዉ። እግዚአብሔር ንፁ ያልሆኑ ሰዎችን ወደ ቤቱ አያስገባም ልጆቹም አድርጎ አይቀበልም ! ስለዚህ ልጅነታችን መፅደቃችንን ተከትሎ የሚመጣው ። Adoption የመጽደቃችን ጠንካራው ማረጋገጫ ነው ።

**– Adoption ማለት ምን ማለት ነው?**

እንግዳን የሆነ ወይንም ከእኛ ጋር ምንም አይነት ግኑኝነት የሌለውን ሰው ወደ ቤታችን የምናስገባበት ደግሞም እንደ ቤተሰብ የምንንከባከብበት እናም የእኛን ውርስ እንደ ልጆች አድርገን የምናወርሰበት ሂደት ነው ። ሌሎች አካላት በቤተሰቦቻችን ውስጥ ቀላቅለናቸው ውርስ ላንሰጣቸው እንችላለን ለምሳሌ የቤት ሰራተኞችን ። ቀድሞ በነበረውም የግሪኮ ሮማን ዘመን በደንብ የሚታወቅ ነው ። አንድ ሰው እናት ወይንም አባት መሆን ከፈለገ የሌላን ሰው ልጅ የራሱ አድርጎ የሚወሰድበት ስርአት ማለት ነው ። ሰዎች ሰዎችን በጉዲፈቻ /ማደጎ ይወስዱ ነበር ህፃናት የሆኑትንም ያልሆኑትንም ። ይህም ህጋዊ በሆነ መንገድ ነው ። በጣም የሚገርመው Adopt የሚደረገው ልጅ Adopt የሚያደርገውን አባት አይመርጥም ። Adopt የሚያደርገው አባት ነው Adopt የሚደረገውን ልጅ የሚመርጠው ።

ጉዲፈቻ የኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ በእምነት ከተመረጡት ቀዳሚ ጥቅሞች አንዱ ነው። በማጽደቅ፣ እግዚአብሔር በደለኛ ኃጢአተኞችን በመለኮታዊ ሕግ ፍርድ ቤት በፊቱ ጻድቅ አድርጎ በማወጅ ይፈርዳል። በጉዲፈቻ፣ ያጸደቁትን የሚወዳቸውን ልጆቹን ያደርጋቸዋል። ልክ እንደ መጽደቅ፣ ጉዲፈቻ አንድ ጊዜ ለመጨረሻ ጊዜ የማይደገም የእግዚአብሔር ተግባር ነው።

እግዚአብሔርን ማወቅ በሚለው ላይ ጄ.አይ ፓከር "አንድ ሰው ክርስትናን ምን ያህል እንደተረዳ ለመገመት ከፈለጋችሁ የአምላክ ልጅ ሰለመሆኑ እና አምላክን እንደ አባቱ አድርጎ ሰለመያዙ ምን ያህል እንደሚያሰብ ይወቁ" ብሏል።

**– በብሉይ ኪዳን የ Adoptionንን Concept በተወሰነ መጠን እናገኛለን ።**

እግዚአብሔር እስራኤልን ልጄ ብሎ ጠርቷል ። ለምሳሌ ፦ — ዘጸአት 4፥23 (አዲሱ መ.ት)""ያመልከኝ ዘንድ ልጄን ልቀቀው" ብዬህ ነበር፤ አንተ ግን እንዳይሄድ ከለከልኸው፤ ስለዚህ የበኵር ልጅህን እገድላለሁ።' "" ይህ የእስራኤል ህዝብ እንደ ህዝብ ልጅ ተብሎ ተጠርቷል ። ነገርግን ልጅነትን እንዴት ነው ያገኙት ? አስቀድሞም ልጆች ነበሩ ?

እግዚአብሔር እስራኤላውያን ሲጠራት በግብፅ በባርነት ስር ነበረች የእግዚአብሔር ልጅ እንድትሆን ጠራት ። –
ሕዝቅኤል 16 (አዲሱ መ.ት) ። 1 የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፤ 2 "የሰው ልጅ ሆይ፤
ለኢየሩሳሌም አስጸያፊ ተግባሯን ፊት ለፊት ንገራት፤ 3 እንዲህም በል፤ 'ጌታ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን
እንዲህ ይላታል፤ 'ዘርሽና ትውልድሽ ከከነዓን ምድር ነው፤ አባትሽ አሞራዊ፣ እናትሽም ኬጢያዊት ነበሩ። 4
በተወለድሽበት ቀን እትብትሽ አልተቈረጠም፤ ንጹሕ እንድትሆኚ በውሃ አልታጠብሽም፤ በጨው አልታሸሽም፤
በጨርቅም አልተጠቀለልሽም። 5 በርኅራኄ ዐይን ተመልክቶሽ ወይም አዝኖልሽ ከእነዚህ አንዱን እንኳ
ያደረገልሽ ሰው አልነበረም፤ ይልቁንም በተወለድሽበት ቀን ተንቀሽ ስለ ነበር ሜዳ ላይ ተጣልሽ።

6 " 'እኔም በዚያ ሳልፍ፣ በደምሽ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ስትንፈራገጪ አየሁሽ፤ በደምሽም ውስጥ ተኝተሽ ሳለሽ፣
"በሕይወት ኑሪ!" አልሁሽ። 7 ሜዳ ላይ እንዳለ ቡቃያ አሳደግሁሽ፤ አንቺም አደግሽ፤ ብርቅ ዕንቍ ሆንሽ።
ጡቶችሽ አጐጠጐጡ፤ ጠጕርሽም አደገ፤ ነገር ግን ከእናትሽ ማሕፀን እንደ ወጣሽ ዕርቃንሽን ነበርሽ። 8
"ዳግመኛም በአጠገብሽ በማልፍበት ጊዜ ወደ አንቺ ተመለከትሁ፤ ለመፈቀርም እንደ ደረሰሽ ባየሁ ጊዜ፣
የመጐናጸፊያዬን ዘርፍ በላይሽ ዘርግቼ ዕርቃንሽን ሸፈንሁ። ማልሁልሽ፤ ከአንቺም ጋር ቃል ኪዳን ተጋባሁ፤ ይላል
ጌታ እግዚአብሔር፤ አንቺም የእኔ ሆንሽ። 9 "በውሃ አጥቤ ከደም አጠራሁሽ፤ ዘይትም ቀባሁሽ። 10 ወርቀ ዘቦ
አለበስሁሽ፤ ምርጥ ቈዳ ጫማም አደረግሁልሽ፤ ያማረ በፍታ አለበስሁሽ ውድ መደረቢያም አጐናጸፍሁሽ። 11

በጌጣጌጥ አንቈጠቈጥሁሽ፤ በእጅሽ አንባር፣ በዐንገትሽም ድሪ አጠለቅሁልሽ፤

[12] በአፍንጫሽ ቀለበት፣ በጆሮሽ ጒትቻ፣ በራስሽም ላይ ውብ አክሊል አደረግሁልሽ፤ [13] በወርቅና በብር አጌጥሽ፤ ልብስሽም ያማረ በፍታ፣ ሐርና ወርቀ ዘቦ ነበር፤ ምግብሽም የላመ ዱቄት፣ ማርና የወይራ ዘይት ነበር። እጅግ ውብ ሆንሽ፤ ንግሥት ለመሆንም በቃሽ። [14] እኔ ከሰጠሁሽ ሞገስ የተነሣ ውበትሽ ፍጹም በመሆኑ ዝናሽ በአሕዛብ መካከል ገነነ፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።

እስራኤል የነበረችበት እና እግዚአብሔር ያደረገላትን ሁኔታ ምን እንደሚመስል በግልጽ ያብራራልናል ። ደግሞ ከእዚህ ሁኔታ አንስቶ ልጁ ያደረጋት ። እስራኤላውያን ልጅነትን በፀጋ እንዳገኙ እጅግ ግልጽ ነው ። ይህንን Concept አዲስ ኪዳናችንም ላይ እናገኘዋለን ።

**– አማኞች የእግዚአብሔር ልጆች ከመሆናችን እሰቀድሞ የማን ወይንም የምን ልጆች ነበርን ?**

የዲያቢሎስ ልጆች ፣ የቁጣ ልጆች ፣ የማይታዘዝ ልጅ፣ የጥፋት ልጅ ብሎ ነው የሚጠራን ። ለምሳሌ ፦ — ኤፌሶን 2፥3 (አዲሱ መ.ት) ። “እኛ ሁላችን በአንድ ወቅት የሥጋችንን ምኞት እያረካን፣ መንገዱንም እየተከተልን በመካከላቸው እንኖር ነበር፤ እንደ ሌሎቹም የቍጣ ልጆች ነበርን።”

በእዚህ ክፍል የቁጣል ልጆች መሆናችንንና የቆጣ ልጆችን መገለጫ ይነግረናል ። ማለትም የቁጣ ልጆች መገለጫ የሰጋን ምኞት ማርካትና መንገዱን መከተል ነው ። የእግዚአብሔር ልጆች መገለጫ ደግሞ ዮሐንስ እንደሚነግረን ከእዚህ በተቃራኒ ነው ።  — 1ኛ ዮሐንስ 2፥29 (አዲሱ መ.ት) ። “እርሱ ጻድቅ መሆኑን ካወቃችሁ፣ <u>ጽድቅን የሚያደርግ ሁሉ ከእርሱ እንደ ተወለደ ታውቃላችሁ።”</u>

ከእዚህ በመነሳት ፅድቅን የማያደርግ ሁሉ ከእግዚአብሔር የተወለደ ነው ማለት እንችላለን ። ይህም ማለት አላማኝ የሆኑቱ የእግዚአብሔር ልጆች አይዱ።

— ቲቶ 3፥3 (አዲሱ መ.ት) ። “ቀደም ሲል እኛ ራሳችን ማስተዋል የጐደለን፣ የማንታዘዝ፣ የተታለልን፣ ለተለያየ ምኞትና ምኞት ባሪያ ሆነን የተገዛን ነበርን፤ እየተጣላንና እርስ በርስ እየተጠላላን በክፋትና በምቀኝነት እንኖር ነበር።”

— ዮሐንስ 8፥44 (አዲሱ መ.ት) ። “እናንተ የአባታችሁ የዲያብሎስ ናችሁ፤ የአባታችሁንም ፍላጎት ለመፈጸም ትሻላችሁ። ኃጢአትን ማድረግ የዲያብሎስን ፍላጎት መፈፀም ነው ይላል አይሁዳዊያንን።  ስለዚህ የፍጥረት የቀድሞ ሁኔታ የተገለፀው በእዚህ መንገድ ነው ።

**– እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ የቤዞት ስራ  ምን አደረገን?**

ልጆቹ አደረገን ! ልጅ ተደርገን እንጂ መጀመርያ ልጆች አልነበርንም  ።  — 1ኛ ዮሐንስ 3፥1 (አዲሱ መ.ት) ። “የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን እንድንጠራ አብ አትረፍርፎ ያፈሰሰልን ፍቅር ምንኛ ታላቅ ነው! እኛም እንዲሁ ልጆቹ ነን።  በእዚህ ውስጥ የተለያዩ ነገሮችን መመልከት እንችላለን ። 1ኛ, የእግዚአብሔር ልጆች አልነበርንም ፣ 2ኛ, አሁን ልጆች ሆነናል ። 3ኛ, ልጆች የሆነውም በእግዚአብሔር ፍቅር ብቻ ነው ። ከእዚህ የተነሳ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ተጠርተናል ደግሞም ነን ።

– ዮሐንስ 1 (አዲሱ መ.ት) ። [12] ለተቀበሉትና በሰሙ ላመኑት ሁሉ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው። [13] እነዚህም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ፣ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።

የተሰጠን መብት ልጅ መሆን ነው ። ይህ ማለት ልጆች አልነበርንም ማለት ነው ። ይህንን ልጅነት የምንቀበለውም በክርስቶስ ስም ሰናምን ነው ። ይህ ማለት በክርስቶስ ስም ያላመነ የልጅነት መብት የለውም ወይንም አይቀበልም ።

– ገላትያ 4 (አዲሱ መ.ት) ።[6] ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር፣ “አባ አባት” ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ ወደ ልባችን ላከ። [7] ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ ባሪያ አይደለህም፤ ልጅም ስለ ሆንህ፣ እግዚአብሔር ወራሽ አድርጎሃል።

እዚህ ጋር ከግሪከኛው ወደ አማርኛው ለመተርጎም የሚያስቸግር ነገርግን ለጥናታችን ጠቃሚ የሆነ ቃል እናገኛለን። ቃል በቃል ከተረጎምነው እንደልጆች ሆነናል ነው የሚለዉ። ሌላኛው ደግሞ ልጅ የነበረ ሳይሆን ባርያ የነበረ ነው ። አሁን ግን ልጅ ተደርገሃል እያለ ነው ።

– ኤፌሶን 2፥19 (አዲሱ መ.ት) ። “ከዚህ የተነሣ እናንተ ከቅዱሳን ጋር የአንድ አገር ዜጋ፣ የእግዚአብሔርም ቤተ ሰብ አባል ናችሁ እንጂ፣ ከእንግዲህ ወዲህ መጻተኞችና እንግዶች አይደላችሁም።”

ከዚህ የተነሳ የሚለው አስቀድሞ ክርስቶስ ከሰራላቸው ስራ መነሻ ምክንያት ማለቱ ነው ። ክርስቶስ ምን አደረገ ? አይሁድ እና አህዛብን በሞቱ አስታረቀ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ ። ወይም በሌላ አገላለጽ እግዚአብሔር ወዳለበት ወደ መቅደሱ በክርስቶስ ደም አማካኝነት እንዲገቡ አደረገ ። ከዚህ የተነሳ እናንተ የሚለው ኤፌሶንያዊያንን ነው ። መስቀሉጨበእዚህ ቁጥር ቢያንስ ሁሉት ነገር አድርጓቸዋል ። 1ኛ, የአንድ አገር ዜጋ ፣ 2ኛ, የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ።

**– የኢየሱስ ክርስቶስ ልጅነት እና የእኛ ልጅነት**

የክርስቶስ ልጅነት

– ዮሐንስ 5 (አዲሱ መ.ት) ። [17] ኢየሱስም፣ “አባቴ እስካሁን እየሠራ ነው፤ እኔም ደግሞ እሠራለሁ” አላቸው። [18] እንግዲህ አይሁድ፣ ኢየሱስ ሰንበትን ስለሻረ ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን አባቱ በማድረግ፣ ራሱን ከእግዚአብሔር እኩል በማድረጉ፣ ሊገድሉት አጥብቀው ይፈልጉት ነበር።

ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጅ የሚለው Concept አምላክ መሆኑን የሚያመለክት ነው ። ዮሐንስ ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ ነው ሲል ከእግዚአብሔር እኩል እግዚአብሔር የሆነ ማለቱ ነው ። – ዕብራውያን 1 (አዲሱ መ.ት) ።[1] እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በተለያየ ጊዜና በልዩ ልዩ መንገድ በነቢያት በኩል ለአባቶቻችን ተናግሮ፣ [2] በዚህ መጨረሻ ዘመን ግን ሁሉን ወራሽ ባደረገውና ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ ለእኛ ተናገረን። [3] እርሱ የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅ ቅና የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ ሆኖ፣ በኀያል ቃሉ ሁሉን ደግፎ ይዞአል፤ የኀጢአት መንጻት ካሰገኘ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ። [4] ስለዚህ የወረሰው ስም ከመላእክት ስም እንደሚበልጥ ሁሉ፣ እርሱም ከመላእክት እጅግ የላቀ ሆኖአል። [5] እግዚአብሔር፣ “አንተ ልጄ ነህ፤ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ፤” ወይስ ደግሞ፣ “እኔ አባት እሆነዋለሁ፤ እርሱም ልጅ ይሆነኛል” ያለው ከመላእክት ከቶ ለማን ነው?

ልጁን ሲገልፅ

**1ኛ, ሁሉን ወራሽ**

**2ኛ, አለማትን የፈጠረ**

**3ኛ, የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራ**

**4ኛ, የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ**

**5ኛ, በኀያል ቃሉ ሁሉን ደግፎ የያዘ**

**– 1ኛ ሁሉን ወራሽ**

በዚህ ሀሳብ ውስጥ ሁለት ነገሮችን እናገኛለን ። ሁሉን ወራሽ ለሚለው የተጠቀመው የግሪክ ቃል τίθημι (ታይቴሚ) የሚል ነው ። የእርሱ ያልሆነን ነገር ተቀብሎ መውረስ ሳይሆን ከመጀመሪያውም ባለቤት መሆኑን የሚያሳይ ቃል ነው ። የሁሉ ባለቤት የሆነው እሱ ነው ሁሉን የወረሰው ።

2ኛ, ስለ ውርስ ማውራቱ በአባት እና በልጅ ወይንም በቤት ውስጥ ስላለው ርስት መከፋፈል የሚዳስስ ነው ። ለምሳሌ ፦ በእኛ ቤተሰብ ውስጥ ብዙ ልጆች አሉ፡፡ ወላጆቻችን ብዙ ሀብት እና ንብረት ኖሯቸው ቢሞቱ ንብረቱን ሁላችንም ነው የምንወርሰው እንጂ እኔ ብቻዬን ሁሉንም ንብረት አልወርስም ። ብቻዬን መውረስ የምችለው የቤቱ ብቸኛ ወይንም አንድያ ልጅ ስሆን ነው ። ኢየሱስ ሁሉን ወራሽ መሆኑ አንድያ ልጅ መሆኑን የሚያሳይ ነው ። ይህም በእኛ ልጅነት እና በኢየሱስ ልጅነት መካከል ልዩነት እንዳለ የሚያሳይ ነው ። ኢየሱስ ሁሉን ከወረሰ በኃላ እካፍሎን እንጂ እኛም እንደ ኢየሱስ ድርሻ ኖሮን አይደለም ።

የእኛን ልጅነት ግን የዕብራውያን ፀሀፊ እንዴት እንደሚገልፅ እንመልከት ። – ዕብራውያን 12 (አዲሱ መ.ት) ። [5] ልጆች እንደመሆናችሁ እንዲህ በማለት የተናገራችሁን ማበረታቻ ቃልም ረስታችኋል፦ “ልጄ ሆይ፤ የጌታን ቅጣት አታቃል፤ በሚገሥጽህም ጊዜ ተስፋ አትቍረጥ፤ [6] ምክንያቱም ጌታ የሚወደውን ይገሥጻል፤ እንደ ልጅ የሚቀበለውንም ይቀጣል።”

**2ኛ, አለማትን የፈጠረ**

እዚህ ጋር አለማትን የፈጠረ ማለት ሰማይን እና ምድርን ያኖረ ማለት አይደለም ። እንደዚያ ቢሆን ኖሮ κόσμος (ኮሰሞስ) የሚል ቃል ነው የሚጠቀሙ ። ነግርግን እዚህ ክፍል ላይ αἰών (አዮን) የሚል የግሪክ ቃል ነው የተጠቀመው ። ይህ ማለት ሰማይ እና ምድር ከተፈጠሩበት ጊዜ ጀምሮ ዳግም እስከሚታደሱበት ጊዜ ድረስ ያለውን ዘመን ቆጥሮ የሰጠ ማለት ነው ። ማለትም ለእነሱ ከሀምሳ ምናምን በፊት የነበረ አንድ አይሁዳዊ እና ለ33 አመት ኖሮ የሞተ ተራ ሰው እንዳልሆነ እያብራራላቸው ነው ። የሰማይና የምድርን እንዲሁም የዕምነት አባቶችን እድሜ ሁሉ ቆጥሮ የሰጠው እርሱ ነው እያላቸው ነው ።

ይህ ከሐዋርያት ስራ 17: 22-26 ካለው አገላለፅ ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነው ።

ሐዋርያት 17 (አዲሱ መ.ት) ። [22] ስለዚህ ጳውሎስ በአርዮስፋጎስ በተሰበሰበው ሕዝብ መካከል ቆሞ እንዲህ አለ፤ “የአቴና ሰዎች ሆይ፤ በማናቸውም ረገድ፣ በጣም ሃይማኖተኞች መሆናችሁን አያለሁ፤ [23] እየተዘዋወርሁ ሳለሁ፣ የምታመልኳቸውን ነገሮች ሰመለከት፣ ‘ለማይታወቅ አምላክ’ የሚል ጽሑፍ ያለበት አንድ መሠዊያ አይቻለሁና፤ እንግዲህ ይህን ሳታውቁ የምታመልኩትን እገልጽላችኋለሁ። [24] “ዓለምንና በውስጡ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነው፤ ስለዚህም እርሱ የሰው እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም። [25] እርሱ ለሰዎች ሁሉ ሕይወትንና እስትንፋስን እንዲሁም ሌላውንም ነገር ሁሉ የሚሰጥ ስለ ሆነ፣ የሚጐድለው ነገር ባለመኖሩ በሰው እጅ አይገለገልም። [26] የሰውን ዘር ሁሉ ከአንድ ወገን ፈጥሮ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ አደረገ፤ የዘመናቸውን ልክና የመኖሪያ ስፍራቸውንም ዳርቻ ወሰነላቸው።

**3ኛ, የእግዚአብሔር የክብር ነፀብራቅ**

ይህ ቃል በመፃፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ጊዜ ነው የተጠቀሰው άπαύγασμα **አፓአጎዝማ** የሚል ነው ። ይህ አገላለጽ ዮሐንስ 1:14 ላይ ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው ። — ዮሐንስ 1፥14 (አዲሱ መ.ት) ። "ቃልም ሥጋ ሆነ፤ በመካከላችንም አደረ፤ እኛም ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ ከአባቱ ዘንድ የመጣውን የአንድያ ልጅን ክብር አየን።"

ፍጥረት በሙሉ በእግዚአብሔር ክብር ፊት መቆም አይችልም ፣ እግዚአብሔርን ማየት አይችሉም ። — 1ኛ ጢሞቴዎስ 6፥16 (አዲሱ መ.ት) ። "እርሱ ብቻ ኢመዋቲ ነው፤ ሊቀረብ በማይቻል ብርሃን ውስጥ ይኖራል፤ እርሱን ያየ ማንም የለም፤ ሊያየውም የሚችል የለም። ለእርሱ ክብርና ኀይል ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን፤ አሜን።" የማይታየው እግዚአብሔር እና የእግዚአብሔር ክብር በክርስቶስ ኢየሱስ ታይቷል ። ይህ ድንቅ የመለኮት አሰራር ነው ፣ እኛም ከእግዚአብሔር ምህረት የተነሳ የእርሱ ሆነናል ።

**4ኛ, የባህሪው ትክክለኛ ምሳሌ**

ይህ አገላለጽ የኢየሱስን አምላክነት በግልጽ የሚያሳይ ነው ። ፈጣሪን በፍጥረት መመሰል አንችልም ። ምናልባትም ፈጣሪን ለመግለፅ አንዳንድ ፍጥረታዊ ነገር ልንጠቀም እንችል ይሆናል ፈጣሪን በትክክል የሚገልፅልን ምሳሌ ግን እራሱ ፈጣሪ ብቻ ነው ።

ጳውሎስም በ ቆላስይስ መፅሐፉ ላይ ይህንን አይነት አገላለጽ ይጠቀማል ። **— ቆላሲይስ 2፥9 (አዲሱ መ.ት) ። "የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካል በእርሱ ይኖራልና፤"** እግዚአብሔርን ሙሉ በሚሉ የገለፀው እየሱስ ብቻ ነው ። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ክብር ነፀብራቅ ብቻ አይደለም እርሱ እራሱ እግዚአብሔር ነው ። አብ እራሱ በዚህም ምድር ቢመጣ ኢየሱስ የኖረውን ኑሮ ነው የሚደግመው ። ይህን ያህል ኢየሱስ መለኮትን ገልጦታል ። ኢየሱስ አምላክን ለመምሰል አይሸመድድም እርሱ እራሱ አምላክ ነው ።

**5ኛ, በኃያል ቃሉ ሁሉን ደግፎ ይዟል !**

በግሪኮች አትላሰ የሚባል አምላክ አላቸው ። ይህ አትላሰ የተባለው አምላክ አለማትን በተከሻው እንደተሸከመ ያምናሉ ። ኢየሱስ ግን አላማትን እንደተሸከመው አትላሰ አይደለም ። እርሱ ነገሮችን ለመፍጠርም ሆነ በስርአቱ ለማስተዳደር ቃሉ ብቻ ሀያል እና ባለስልጣን ነው ። መዝሙር መፅሐፍ ላይ አለማት በእርሱ ንግግር እንደ ተፈጠሩ እና እንደፀኑ ይናገራል ። — መዝሙር 33 (አዲሱ መ.ት)[7] የባሕርን ውሃ በአንድ ዕቃ ይሰበስባል፤ ቀላዩንም በአንድ ሰፍራ ያከማቻል። [8] ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን ትፍራው፤ በዓለም የሚኖር ሕዝብ ሁሉ በፊቱ ይንቀጥቀጥ። [9] እርሱ ተናግሮአልና ሆኑ፤ አዘአልና ጸኑም።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ልጅ የሆነው ሲወለድ አይደለም ፣ አምኖም አይደለም ፣ በትንሳኤውም አይደለም ከዘለአለም በፋት ነው ። የባህሪ ልጅነት እና የፀጋ ልጅነት ። የእኛ ልጅነት የባህሪ ልጅነት አይደለም የፀጋ ልጅነት እንጂ ።

## Sanctification/ መቀደስ

በ order of salivation Sanctification ከ Justification ተከትሎ መምጣቱ የነገረ ድነትን እውነታ በግልጽ እንድንመለከት ያደርገናል ። ይህ ማለት መፅደቃችን የእኛን የእየተለተለት ለውጥ ወይንም የእኛን ስራ ተከትሎ የሚመጣ ነገር እንዳልሆነ በግልጽ የሚያመለክት ነው ። እኛ የምንፀድቀው በእኛ ስራ ሳይሆን ክርስቶስ

ለእኛ በሰራው ስራ ነው ። የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ፅድቅን በ declaration ሳይሆን በ Infusion ስለምትረዳ መፅደቅ ከመቀደስ በኋላ የሚመጣ ነገር ነው ብላ ታስተምራለች ። እኛ ደግሞ መቀደስ ፅድቅን ተከተሎ የሚመጣ ነገር ነው እንላለን ። ይህም ማለት ያልፀደቀ ሰው መቀደስ አይችልም ደግሞም የፀደቀ ሰው አለመቀደስ አይችልም ። ሁሉቱ በፍፁም ሊነጣጠሉ አይችሉም ። ነገር ግን ሁለቱ የተለያየ ትኩረት አላቸው ። Justification የእኛን ህጋዊ ሁኔታ እንጂ እኛን ስለመለወጥ አይደለም ትኩረቱ ። Sanctification ደግሞም የእኛን ህጋዊ ሁኔታ መለወጥ ሳይሆን እኛን መለወጥ ነው ። ይህ ከገባን በ Justification እና በ Sanctification መካከል ያለው ልዩነት ገብቶናል ።

ከእዚህ ጋር ተያይዞ ሁለት የተለያዩ ፅንፎች አሉ ። አንደኛው legalism ሲሆን ይህም ድነት ወይንም ፅድቅ በህግ ስራዎች ነው የሚገኘው የሚል ነው ። ሌላኛው ደግሞ Antinomianism የሚበላል ነው ። ይህም ሰው ከዳነ በኋላ ሙሉ በሙሉ ከህግ ስራዎች ነፃ ሆኗል ማለት ነው ይላሉ ። ሁለቱም አደገኛ አመለካከቶች ብቻ ናቸው ሳይሆን ከድነትም ያጎላሉ ። ይህንን ማለት Dispensationalism እንደ Antinomian ናቸው ማለት አይደለም ። መፅሐፍ ቅዱስ ግን በግልጽ የሚነግረን በብጎ ስራዎች ወይንም በህግ ስራዎች አልዳንንም ። ነገርግን ለበጎ ስራዎች ድነናል ።– ኤፌሶን 2 (አዲሱ መ.ት) ። ⁹ ማንም እንዳይመካ በሥራ አይደለም፤ ¹⁰ ምክንያቱም፣ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ እንድንሠራ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን።

Luther እንደዚህ ይላል ፦ "**We are saved by faith alone, but the faith that saves is never alone"**

መቀደስ የአማኞች ዋነኛው መለያ ነው ። ያላመኑ ሰዎች መቀደስ ስለማይችሉ መቀደስ የአማኞች ብቻ ይሆናል ማለት ነው ።Luther እንደዚህ ይላል ፦ "We are saved by faith alone, but the faith that saves is never alone"

ደግሞም በጣም የሚገርመው በ order of salivation ከ Adoption በኋላ Sanctification መምጣቱ በተወሰነ መጠን ለእግዚአብሔር መቀደስ የ ቤተሰብ Rule አድርገን እንድናስብ ያደርገናል ። ይህም Rule ደግሞ የእግዚአብሔር ቤት ለመግባት የሚደረግ ሳይሆን ወደ ቤቱ ስለገባን የምንጠብቀው Rule ነው ። የእግዚአብሔር ቤት ለመግባት ህግ መጠበቅና የእግዚአብሔር ቤት ስለገባን የምንጠብቀው ህግ ይለያያል ።

ይህ ማለት በሌላ አገላለጽ ለእግዚአብሔር ለመገዛትና ኃጢአትን የማናደርግበት ምክንያት የልብ ዝንባሌአችን ስለተለወጠ ነው ። እግዚአብሔርን የምንታዘዝበት ምክንያት ወይንም ኃጢአት ላለመስራት የምንፈጥርበት ምክንያቱም እግዚአብሔርን ስለምንወድ ነው ። ሲኦልን ሞትን ስለምንፈራ አይደለም ምክንያቱም ሲኦል ተወግዷል ሞት ተወግዷል ።

**– Sanctification ምን ማለት ነው ?**

Sanctification ከ Latin የተገኘ ቃል ሲሆን ትርጉሙም **"to make holy."** ማለት ነው ወይንም Holines or Separation የሚለዉ ይገልፀዋል ። paul washer እዚህ ጋር ቆንጆ ምሳሌ ይሰጣል ። የሂብሩ ቃል **to cut** ማለት ነው ይልና ሚስቱን እንደምሳሌ አድርጎ ይጠቅሳል ። ባለቤቴ ምግብ ማብሰል ትወዳለች በ table ላይ ለመክተፍ የፈለገችውን ነገር ታስቀምጥና በፍጥነት መክተፍ ትጀምራለች ። እየከተፈች የተከተፈውን ካልተከተፈው ትለየዋለች ይላል ። እግዚአብሔርም ስለ ቅድስና ሲያወራ ልክ እንደዚያው ነው ይላል ።

እግዚአብሔር እኛን ከምን ይለየናል ? ከየትኛውም እግዚአብሔርን ከሚቃረን አስተሳሰብ እና ድርጊት ይለየናል ። ቅድስና እግዚአብሔርን ከሚቃረን ከየትኛውም ነገር ማምለጥ ከእዚያም ወደ እራሱ ወደ እግዚአብሔር ማምለጥ ነው ። **ቶማስ ዋትሰን ፦ ኃጢአት መራር ካልሆነችልን ክርስቶስ ጣፋጭ አይሆንልንም ይላል ።**

መቀደስ በብሉይ ኪዳን በሰፋት የምናገኘው አካላዊ ከሆኑ ንክኪዎች የተያያዙናቸው ። ለምሳሌ ፦ ከጊዜ ፣ ከቦታ ፣ ከእቃ ከሰው ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ናቸው ። በተለይም ከመንፃት ስረአት ጋር የተገናኘ ነው ። አዲስ ኪዳን ላይ ግን በዋናነት ወደ ውስጥ ወደ ልብ የጠለቀን መለየት የሚያመለክት ነው ።

መፅሐፍ ቅዱስ መቀቀደስን በሀላፉ በአሁን ጊዜና በወደፋት ይገልፀዋል ። ሶስቱንም በእየአውዱ መረዳት ከሰህተት ይጠብቀናል ።

**1ኛ, positional sanctification,**

ይህ ከ Justification ጋር ተመሳሳይ ነው ። Union with Chris በመሆናችን ያገኘነው ቅድስና ነው ። **— 1ኛ ቆሮንቶስ 6፥11 (አዲሱ መ.ት) ። "ከእናንተ አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ ነበራችሁ፤ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፤ <u>ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል።"</u>** ይህ የአላፊ ጊዜ መሆኑ ግልጽ ነው ። ተቀደሱ ከሚለውም ቀጥተኛ መመሪያ የተለየ ነው ። ደግሞም የቆሮንቶሱ አውድን አውድ ከተመለከትን አማኞች በሆኑና አማኞች ባልሆኑ ሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት የሚያነሳ ነው ። ይህኛው መቀደሰ አማኞች ካልሆኑ ሰዎች አማኝ በመሆናቸው ምክንያት መለየታቸውን የሚያመለክት ነው ።

**– ዕብራውያን 10 (አዲሱ መ.ት) ። ⁹ ቀጥሎም፣ "እነሆኝ፤ ፈቃድህን ለማድረግ መጥቻለሁ" አለ፤ ሁለተኛውን ለመመሥረት የመጀመሪያውን ሻረ። ¹⁰ በዚህ ፈቃድ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ አማካይነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በቀረበው መሥዋዕት <u>ተቀድሰናል</u>።** ይህም የህላፊ ጊዜ ነው ።

በጠቅላላው positional sanctification ሀሳብ የክርስቶስ አካል በመሆናችን ምክንያት የክርስቶስ ቅድስና ተካፋዮች መሆናችንን ነው ። እዚህ ጋር የሁሉም ክርስቲያኖች ቅድስና እኩል ነው ። ይህ ቅድስና በፆምና በፀሎት መፅሐፍ ቅዱስን በማንበብ የተለያዩ ኃይማኖታዊ ሰርአቶችን በመፈፀም የሚገኝ አይደለም ። ደግሞ ሰነ መለኮት የተማረም ያልተማረም በእኩል የሚያገኙት የቅድሰና አይነት ነው ። በጌታ ቤት ለእረጅም አመት የቆየ ደግሞም ያልቆየ ደግሞም አገልጋይ የሆነ ደግሞም ያልሆነ ያው ነው ቅድሰናቸው ። ይህ ቅድስና የሚጨምርም የሚቀንሰም ቅድሰና አይደለም ። ለአንዴ የሆነ ነገርግን የመጨረሻ ቅድሰና ነው ።

**2ኛ, progressive (Experiential) sanctification,**

ይህ የቅድሰና አይነት እንደ positionalኡ የአንዴ ጊዜ ሳይሆን ሂደታዊ ነው ።

ማለትም ደግሞ ከተወለድንበት ጊዜ አንሰቶ ክርሰቶስ ዳግም እሰከሚመጣበት ጊዜ ድረሰ የምንለማመደው የቅድሰና አይነት ነው ። በክርሰቶስ ሳናምን የነበረንን ባህሪና ድርጊት ለማሰወገድ የምናደርገው ጥረት እንዲሁም የክርሰቶሰን አይነት አዲሱን ህይወት ለመኖር የምናደርገው ትግል ነው ይህ የቅድሰና አይነት ።

**1ኛ ጴጥሮስ 1 (አዲሱ መ.ት) ።¹³ ስለዚህ ልባችሁን አዘጋጁ፤ ራሳችሁንም ግዙ፤ ተስፋችሁን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ ለእናንተ በሚሰጠው ጸጋ ላይ ሙሉ በሙሉ አድርጉ። ¹⁴ ታዛዦች ልጆች እንደመሆናችሁ መጠን ቀድሞ ባለማወቅ ትኖሩበት የነበረውን ክፉ ምኞት አትከተሉ። ¹⁵ ነገር ግን የጠራችሁ እርሱ ቅዱስ እንደሆነ**

**እናንተም በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ፤ [16] ምክንያቱም “እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ” ተብሎ ተጽፎአል።** የእግዚአብሔር ቅድስና ከማንነቱ ጋር የተያያዘ ነው ። የአማኞች ቅድስና ግን በክርስቶስ በመሆናቸው የሚመነጭ ነው ። እግዚአብሔር ከፍጥረቱ የተለየ እንደሆነው ሁሉ አማኞችም በኑሮአቸው ከማያምኑ ሰዎች ሊሆኑ ይገባቸዋል ።

progressive sanctification ከኃጢአት ጋር ብቻ ሳይሆን ከሀሰተኛ አስተማሪዎች ጋር እና ከስህተት ትምህርት ጋር መለየትን አይይዙት መፅሐፍ ቅዱሳችን ይነግረናል ።

2ኛ ቆሮንቶስ 6 (አዲሱ መ.ት) ።[14] ከማያምኑ ሰዎች ጋር አግባብ ባልሆነ መንገድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዐመፅ ጋር ምን ግንኙነት አለው? ብርሃንስ ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?

[15] ክርስቶስ ከቤልሆር ጋር ምን ስምምነት አለው? የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ኅብረት አለው? [16] የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከጣዖታት ጋር ምን ስምምነት አለው? እኛኮ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነን፤ እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል ተናግሮአል፤ “ከእነርሱ ጋር እኖራለሁ፤ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፤ አምላካቸው እሆናለሁ፤ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ።”

[17] “ስለዚህ ከመካከላቸው ውጡ፤ ለእኔም የተለያችሁ ሁኑ፤ ይላል ጌታ። ርኩስ የሆነውን ነገር አትንኩ፤ እኔም እቀበላችኋለሁ።”

[18] “እኔ አባት እሆናችኋለሁ፤ እናንተም ወንዶችና ሴቶች ልጆቼ ትሆናላችሁ፤ ይላል ሁሉን የሚችል ጌታ።”

— 2ኛ ቆሮንቶስ 7፥1 (አዲሱ መ.ት) ። “እንግዲህ፣ ወዳጆች ሆይ፤ ይህ የተሰፋ ቃል ስላለን፣ ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ነገር ሁሉ ራሳችንን እናንጻ፤ እግዚአብሔርንም በመፍራት ቅድስናችንን ፍጹም እናድርገው።”

ከማያምኑ ጋር የሚሆው ለይቶላቸው አማኝ ያልሆኑ ሰዎችን እያወራ አይደለም ። ይህንን በሁለት ምክንያቶች መረዳት እንችላለን ። 1ኛ, የሁለተኛ ቆሮንቶስ አውድ የተፃፈበትን አውድ በመመልከት ። ይህም ከሀሰተኛ አስተማሪዎች ጋር የተያያዘ ነው ። እነዚህም ሀሰተኛ አስተማሪዎች ሐዋሪያት ሳይሆኑ እራሳቸውን እንደ ሐዋሪያት የሚቆጥሩና የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው የሚሸቅጡ ናቸው ። — 2ኛ ቆሮንቶስ 2፥17 (አዲሱ መ.ት) ። “እኛኮ ትርፍ ለማግኘት ብለን የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት እንደ ብዙዎቹ አይደለንም፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር እንደተላኩ ሰዎች በክርስቶስ ሆነን በእግዚአብሔር ፊት በቅንነት እንናገራለን።”

2ኛ, በቁጥር 17 **ከመካከላቸው ውጡ** የሚለው ለይቶላቸው ውጪ ያልሆኑ ሰዎች እንደሆነ የሚገልጽ ነው ። ለእዚህም ነው ተለዩ ፣ ተቀደሱ የሚለው ። ስለዚህ ከሀሰተኞች እና ከስህተት ትምህርት መለየትንም መፅሐፍ ቅዱስ ቅድስና ብሎ ይጠራዋል ።

መዕራፍ ሰባት ላይ ደግሞ የስህተት አስተማሪዎች ስጋን እና መንፈስን ያረክሳሉ ስለዚህ መቀደስ ከእዚያ ነገር መራቅ ነው ። ግን ደግሞ ከሀሰተኛ አስተማሪዎች እና ከስህተት ትምህርት ጋር የተያያዘ ብቻ አይደለም ። ከኃጢአት ጋርም የተያያዘ ነው ። ይህንን **ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ነገር ሁሉ ራሳችንን** በሚለው አረፍተ ነገር መረዳት እንችላለን ።

በመሰረቱ ይህንን አይነት የቅድስና ህይወት የሚኖሩት አስቀደሞ የተቀደሱ ሰዎች ናቸው ። ለክርስቶስ ያልተለየ ለክርስቶስ ሊኖር አይችልም ። ይህም ቅድስና በአጭሩ በቆሸሸው አለም ውሰጥ በንፅህና መኖር ነው ።

**ደህንነት ከእርጌው ስርዓት ነፃ መውጣት ብቻ ሳይሆን የአዲሱ ህይወት ጅማሬም ነው ።** የክርስቶስ የመስቀሉ ስራ አማኞችን ከሀጥያት ባርነት ነጻ ማድረግ ብቻ ሳይሆን የፅድቅም ባርያ የማድረግ ሀይል አለው ። — 1ኛ ጴጥሮስ 1፥2 (አዲሱ መ.ት) ። “እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ ካወቃቸው፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመታዘዝ በደሙ ለተረጩትና በመንፈስ አማካይነት ለተቀደሱት፤ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።”

በጠቅላላው progressive sanctificationንን በሁለት አቅጣጫ መመልከት እንችላለን ።

1ኛ, ከክርስቶስ ሞት ጋር በመተባበር ለኃጢአት እና ለክፋት ሁሉ መሞት ። 2ኛ, የክርስቶስ ትንሳኤ ተካፋዮች በመሆን ለአዲስ ህይወት መኖር ።

መቀደስ አማኞች በኃጢአት እና በክፉው አለም ላይ ያላቸውን ድል የሚያመለክት ነው ። አማኞች ሁሉ የሚታገሏቸው ሶስት ጠላቶች አሏቸው ። አለም ስጋና ሰይጣን ናቸው ። ከኃጢአት ጋር ጦርነት ውስጥ ነው ያለነው ካልታገልነው እኛን ለማጥፋት ነው የሚሰራው ። የአማኞች የቅድስና የመጨረሻውም ውጤት ክርስቶስ ኢየሱስን መምሰል ነው ።

### 3ኛ, final (Ultimate ) sanctification.

ይህ ደግሞ ከ Glorification ጋር ተመሳሳይ ነው ። ይህ ከመሞታችን እና ከትንሳኤ አካል ጋር የተያያዘ ነው ።

– 2ኛ ቆሮንቶስ 5 (አዲሱ መ.ት) ።[6] ስለዚህ ሁል ጊዜ በመታመን እንኖራለን፤ በሥጋ እስካለን ድረስ ከጌታ ርቀን እንደምንገኝ እናውቃለን፤ [7] ምክንያቱም የምንኖረው በእምነት እንጂ በማየት አይደለም። [8] <u>ከሥጋ ተለይተን</u> ከጌታ ጋር መኖርን እንደምንመርጥ ርግጠኛ ሆኜ እናገራለሁ።

– ሮሜ 8 (አዲሱ መ.ት) ።[22] እስከ አሁን ድረስ ፍጥረት ሁሉ በምጥ ጊዜ እንዳለው ሥቃይ በመቃተት ላይ እንደሚገኝ እናውቃለን። [23] እርሱ ብቻ ሳይሆን፣ የመጀመሪያውን የመንፈስ ፍሬ ያገኘን እኛ ራሳችን የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነታችንን በናፍቆት እየተጠባበቅን በውስጣችን እንቃትታለን። [24] በዚህ ተስፋ ድነናል፤ ተስፋው የሚታይ ከሆነ ግን ተስፋ አይደለም፤ የሚያየውንማ ማን ተስፋ ያደርገዋል? [25] ነገር ግን ገና ያላየነውን ተስፋ ብናደርግ፣ በትዕግሥት እንጠብቀዋለን።

– ፊልጵስዩስ 3 (አዲሱ መ.ት) ። [17] ወንድሞች ሆይ፤ የእኔን አርኣያነት በመከተል ከሌሎች ጋር ተባበሩ፤ እኛ በሰጠናችሁ ምሳሌነት መሠረት የሚኖሩትንም አስተውሉ። [18] ምክንያቱም ከዚህ በፊት ደጋግሜ እንደ ነገርኋችሁ፣ አሁንም እንደ ገና፣ ያውም በእንባ እነግራችኋለሁ፤ ብዙዎች የክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ሆነው ይመላለሳሉ። [19] መጨረሻቸው ጥፋት ነው፤ ሆዳቸው አምላካቸው ነው፤ ክብራቸው በነውራቸው ነው፤ ልባቸው ያረፈው በምድራዊ ነገር ላይ ነው። [20] እኛ ግን አገራችን በሰማይ ነው፤ ከዚያ የሚመጣውንም አዳኝ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በናፍቆት እንጠባበቃለን፤ [21] እርሱም ሁሉን ለራሱ ባስገዛበት ኀይል፣ ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል።

**– በምን ልንቀደስ እንችላለን ?**

በእግዚአብሔር ቃል !

– ዮሐንስ 17 (አዲሱ መ.ት) ።[14] ቃልህን ሰጥቻቸዋለሁ፤ እኔ ከዓለም እንዳይደለሁ፣ እነርሱም ከዓለም

ባለመሆናቸው ዓለም ጠልቶአቸዋል። [15] የምለምንህም ከክፉው እንድትጠብቃቸው እንጂ፣ ከዓለም እንድታወጣቸው አይደለም። [16] እኔ ከዓለም እንዳልሆንሁ ሁሉ፣ እነርሱም ከዓለም አይደሉም። [17] ቃልህ እውነት ነው፤ በእውነትህ ቀድሳቸው። [18] አንተ ወደ ዓለም እንደ ላክኸኝ እኔም ወደ ዓለም ልኬአቸዋለሁ። [19] እነርሱ በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ፣ ራሴን ስለ እነርሱ ቀድሻለሁ።

– ኤፌሶን 5 (አዲሱ መ.ት) [26] በቃሉ አማካይነት በውሃ አጥቦ በማንጻት እንድትቀደሰ፣ [27] እንዲሁም ጉድፍ ወይም የፊት መጨማደድ ወይም አንዳች እንከን ሳይገኝባት ቅድስትና ነውር አልባ የሆነች ክብርት ቤተ ክርስቲያን አድርጎ ለራሱ ሊያቀርባት ነው።

**Justification delivers from the penalty of sin**

**Sanctification delivers from the power of sin**

**Glorification delivers from the presence of sin**

## Perseverance of the Saints/የቅዱሳን ፅናት

በጣም እጅግ ድንቅ Doctrine ነው ። የእግዚአብሔርን የማዳን ውበት እና ታማኝነት በግልጽ የምናይበት ነው ። እግዚአብሔር የወደደን እስከ መቼ እና እስከ ምን ድረስ ነው የሚለውን ፍንትው አድርጎ የሚያሳየን Doctrine ሲሆን ደግሞም ይህ Doctrine በስህተት መንገድ ለመተርጎም የተጋለጠ ስለሆነ አስቀድሞ ምን ማለት አይደለም የሚለውን እንመልከት ። እዚህ ላይ ምን እያልን አይደለም የሚለውን በብዙ መንገድ መግለጽ ይቻላል ግን ሁሉንም ነገር አቅፎ የሚይዝን አንድ ነገር በመግለፅ የተብራራ ሀሳብ ማቅረብ ይቻላል ።

**– የቅዱሳን ፅናት ስንል ምን እያልን አይደለም ?**

- One Saved Always Saved (OSAS) እያልን አይደለም ።

ብዙውን ጊዜ የቅዱሳን ፅናት እና OSAS እንደ አንድ ዓይነት ትምህርት ተደርገው ይወሰዳሉ ። ነገር ግን አንድ አይነት አይደሉም ። ይህ ማለት አንድ የሚያደርጋቸው ነገር የላቸውም ማለት አይደለም ። Perseverance of the Saints እና One Saved Always Saved መካከል ያለውን ልዩነት ብቻ ሳይሆን አንድነትም አለ ። እናም አንድነቱን እና ልዩነቱን በጥንቃቄ መረዳት አለብን ። አንዳንድ ጊዜ ልዩነቱን ለማሳየት ብለን አንድነቱን እናጠፋለን እንዲሁም አንድነታቸውን ለማሳየት ብለን ልዩነታቸውን እናጠፋለን ። ስለዚህ በሁለቱ መካከል ያለውን አንድነት እና ልዩነት በጥንቃቄ መመልከት ጥሩ ነው ። አንዳንድ ሰዎች ቃላቶቹን በተለዋዋጭነት እንደሚጠቀሙበት አስባለሁ ። ነገርግን የበለጠ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት ያሌብን ይመስለኛል።

በ Perseverance of the Saints እና One Saved Always Saved መካከል ያለውን ልዩነት እና አንድነት **W. Robert Godfrey** በጥሩ መንገድ አስቀምጦታል ። የሚያመሳስላቸው ነገር በክርስቶስ አምኖ የፀደቀ ሰው ከድንነት ተቆርጦ አይወጣም በሚለው ሲሆን ይህንን በእኩልነት የምንጋራው እውነት ነው ።

ልዩነታቸው ደግሞ እግዚአብሔር እስከፍፃሜ የሚያደርሳቸው እንዴት ነው በሚለው ላይ ነው ።

– ለምሳሌ፦ Perseverance of the Saints እና One Saved Always Saved መካከል ያለውን ልዩነት እንመልከት

1ኛ,  Perseverance of the Saints የተመሰረተው  በ Unconditional Election ላይ ነው ። እግዚአብሔር አንዳንድ ግለሰቦችን ለዘላለማዊ መዳን አስቀድሞ ወሰኗል፣ እናም እግዚአብሔር እንዲድኑ ስለመረጣቸው ለመፅናት ዋስትና ሰጥቷቸዋል የሚል አመለካከት ሲሆን

በአንጻሩ ደግሞ **OSAS** በምርጫ ትምህርት ላይ የተመሠረተ አይደለም ። ነገር ግን በኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ተስፋ ላይ ነው ።  ደግሞም ምርጫ ለአገልግሎት እንጂ ለዘላለማዊ ሕይወት አይደለም ይላሉ ።

2ኛ,  Perseverance of the Saints እና OSAS ስለ ድነት በተግባር የተለያየ አመለካከት አላቸው።  በ Perseverance of the Saints  መፅደቃችን በማያቋርጥ እምነት እና መልካም ሥራዎችን እንደምናፈራ እናስተምራሩ፣ ይህም ደግሞ እግዚአብሔር ለተመረጡት ብቻ የሚሰጠው “ስጦታ” ነው እንላሉ ።

በአንጻሩ **OSAS** መዳን በኢየሱስ ላይ ባለህ አንድ ነጠላ እምነትን ይጠይቃል ።  እናም ባመንክ ጊዜ የዘላለም ሕይወት ታገኛለህ ። ቀጣይነት ያለው እምነት እና ስራ ለደቀመዝሙርነት እንጂ ከመዳን ጋር ግኑኝነት  የለውም ብለው ያስባሉ ።

3ኛ,   ስለ መቀደስ የተለያዩ አመለካከቶች አላቸው ። በ Perseverance of the Saints  የተመረጡት አስቀድሞ ለድኅነት ስለተወሰኑ፣ እና እግዚአብሔር እንዲቀደሱ ስላደረጋቸው፣ በዚህ ሕይወት ፈጽሞ ወደ ትልቅ ኃጢአት ወይም አለማመን አይወድቁም ነገር ግን በእምነትና በበጎ ሥራ እስከ ሞት ድረስ ጸንተው ይኖራሉ።

በአንጻሩ **OSAS** መቀደስ እንዳለብን ቢያምኑም  ነገር ግን አማኞች ተግባራዊ ቅድስና ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም ዘላለማዊ ደህንነታቸው የተጠበቀ ነው ብለው ያምናሉ ።

4ኛ,  በ Perseverance of the Saints እና **በ OSAS** ድነታችንን እንዴት ነው የምናረጋግጠው የሚለው ላይ የተለያዩ አፅኖቶች አሏቸው። እዚህ ላይ በትክክል እየተባለ ያለውን መረዳት ትንሽ ከባድ ነው ። በተሳሳተ መንገድ እንዲተረጎም በር የሚከፍት ነው ።

በ Perseverance of the Saints መዳንህን አምኛለሁ ስላልክ ብቻ እርግጠኛ መሆን አትችልም  ። ምክንያቱም ልዩ የጸጋ እምነት ካላቸው ከተመረጡት መካከል መሆንህን እርግጠኛ መሆን አትችልም በእምነት እና በበጎ ስራ እስካልፀና ድረስ እንላለን ።

በአንፃሩ **ለOSAS** ደህንነትን ማረጋገጥ የሚቻለው እምነትን የማዳን ዋና ነገር ነው ። ኢየሱስ ለአማኞች የዘላለም ሕይወት ቃል ገብቷል። ስለዚህም እርሱ የሚሰጠውን ሕይወት ዘላለማዊ እንደሆነ ካመንክ ደግሞ ትችላለህ ነው የሚሉ ።

የ OSAS አገላለጽ የ Antinomian ይመስላል ። ምክንያቱም አሁን ስለዳንኩ እኔ በፈለኩት መንገድ መኖር እችላለሁ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። አብዛኞቹ ሰዎች  ግን OSAS ሲሉ ይህንን ማለታቸው አይደለም ። ነገር ግን OSAS ማለታቸው አሳሳቢ እና ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ እንዳለ ለማየት ችያለሁ።

በሌላ በኩል፣ የቅዱሳን ጽናት እንደ ቅዱሳን በመጽናት እንደምንኖር ያሳስባል—እንደ ቅዱሳን እየኖርን ቅድስናን እየተከተልን እና በእምነት እንኖራለን። እንደ ክርስቲያናዊ ኑሮ፣ መጽናት አለብን የሚለው አስተምህሮ የበለጠ ጠቃሚ ነው።  በተመሳሳይ ጊዜም የመጽናት ተግባራችንን ድነትን በሥራ መመሰረት ፅድቅን ማግኛ መንገድ እያደረግን እንዳልሆነ ግልጽ ማድረግ አለብን ። ሁልጊዜ ጽናታችንን በእግዚአብሔር ጥበቃ ላይ ካለን እምነት ጋር ማገናኘት አለብን ።

የቅዱሳን ፅናት በራሱ አንድ የሚነግረን ነገር አለ እርሱም የሚፀኑት ቅዱሳን የሆኑት ብቻ ናቸው ። በሌላ አገላለጽ ለይቶላቸው ክርስትናን ክደው ያሉትም ሆነ በክርስትና እምነት ውስጥ ተቀላቅለው እራሳቸውን አማኝ ነኝ ብለው የሚጠሩ ነገር ግን አማኞች ያልሆኑ አይፀኑም ማለት ነው ። — 1ኛ ዮሐንስ 2፥19 (አዲሱ መ.ት) ። "ከእኛ መካከል ወጡ፤ ይሁን እንጂ ከእኛ ወገን አልነበሩም፤ ከእኛ ወገን ቢሆኑማ ኖሮ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር። ነገር ግን ሁሉም ከእኛ ወገን እንዳልነበሩ ይታወቅ ዘንድ ከእኛ ተለዩ።"

የቅዱሳን ፅናት በብዙ መንገድ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተብራርቶ እናገኘዋለን ። ነገርግን በተወሰኑ የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባባት ላይ መሰረት አድርገን ይህንን እውነታ እንመልከት ።

**– በሮሜ መፅሐፍ የቅዱሳን ፅናት እንዴት ተብራራ?**

ይህንን ሀሳብ በግልጽ ተብራርቶ የምናገኘው ከምዕራፍ 8 እስከ 11 ባለው ክፍል ነው ። አስቀድሞ የሮሜን መፅሀፍ ሀሳብ በሀሳብ ከፋፍለን እንመልከተው ።

1ኛ, ከምዕራፍ 1 እስከ 3:1-20 ሰዎች ከኃጢአት ፍርድ በታች መሆናቸውን ያሳያል ይህም ( Total depravity )ብለነው መጥራት እንችላለን ወይም The penalty of sin ብለን መጥራት እንችላለን ።

2ኛ,ከምዕራፍ 3:21 እስ ምዕ 5:20 ከሀጥያት ቅጣት ነፃ መውጣት( Justification)

3ኛ, ከምዕራፍ 6 እስከ 8:17 ። ከኃጢአት ሀይል ጋር መታገል ። ( Sanctification)

4ኛ, ከም 8:18-27 ። ከሀጥያት መገኘት ይንም አለም ነፃ መውጣት ። (Glorification)

5ኛ ከምዕ 8:18-27 እስከ ምዕ 11 እግዚአብሔር ለቃልኪዳኑ ታማኝ ነው (Perseverance of the Saints)

ለጊዜው የእኛን ትኩረት ከምዕራፍ 8:18-27 እስከ ምዕ 11ባለው ላይ ትኩረት እናደርጋለን ።

**– ሮሜ 8፥30 "አስቀድሞ የወሰናቸውን ጠራቸው፤ የጠራቸውን አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውን አከበራቸው።"**
ጳውሎስ እግዚአብሔር የጠራውን እስከ ክብር ያደርሳል የሚል ሙግት ይጀምራል ። ለዚህም ሀሳቡ proof እንዲያደርግለት ቁጥር 32ትን እንደ መሳርያ ይጠቀማል ። — ሮሜ 8፥32 (አዲሱ መ.ት) ። "ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት፣ ነገር ግን ለሁላችንም አሳልፎ የሰጠው እርሱ፣ ሁሉንስ ነገር ከእርሱ ጋር እንደ ምን በልግሰና አይሰጠን?"

እግዚአብሔር የጠራቸውን ክርስቶስን በመስቀል ሰጥቶ የእርሱ ቤተሰብ አባል አድርጓቸዋል ። ታድያ የቀሩትን የተሰፋ ቃሎች እንዴት አይፈፅምም በማለት ሙግቱን ይቀጥላል ። እነዚህ የተቀሩት ተሰፋዎችን በተሳሳተ መንገድ ከምድራዊ ነገር ጋር እያይዘውት ሲተረጉሙ ተመልክቻለሁ ። ነገር ግን የክፍሉን ሀሳብ ተከትለን ከሄድን እግዚአብሔር ልጁን ለእኛ አሳልፎ ከሰጠን እንዴት ቀጣይ በረከቶችን ማለትም የእኛን መፅደቅ እና መክበር አያሳካውም ብለን እንጠረጥራለን እያለ ነው ። ልጁን ሰለ አንተ ኃጢአተኛው ብሎ ከሰጠ አንተን ኃጢአተኛውን እንዴት አያፀድቅም እንዴት አያከብርም እያለ ነው ። በመቀጠል ይህንን ሀሳብ ሁለት ቁጥሮችን ዝቅ ብሎ ማብራራት ይጀምራል ። – ሮሜ 8 (አዲሱ መ.ት) ። ³⁵ ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማን ነው? ችግር ነው ወይስ ሥቃይ፣ ወይስ ስደት፣ ወይስ ረሀብ፣ ወይስ ዕራቍትነት፣ ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ? ³⁶ ይህም፣ "ስለ አንተ ቀኑን ሙሉ ከሞት ጋር እንጋፈጣለን፤ እንደሚታረዱ በጎች ተቈጠርን" ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው። ³⁷ ምንም አይለየንም፤ በዚህ ሁሉ በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን። ³⁸ ይህን ተረድቻለሁ፤ ሞትም ይሁን ሕይወት፣ መላእክትም ይሁኑ አጋንንት፣ ያለውም ይሁን የሚመጣው፣ ወይም ማንኛውም ኀይል፣ ³⁹ ከፍታም ይሁን

ጥልቀት፣ ወይም የትኛውም ፍጥረት፣ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም።

በእነዚህ ቁጥሮች ሰዎች ለሌሎች ሰዎች ካሏቸው ፍቅር ሊለዩ የሚችሉ ናቸው ። ነገርግን ሰዎችን ከሰዎች የሚለዩ ነገሮች ክርስቶስ ለእኛ ካለው ፍቅር አይለየንም ይለናል ። ለምን? ምክንያቱም የክርስቶስ ፍቅር ብርቱ ስለሆነ ። እዚህ ምድር ላያ ካሉ ከማንኛውም ተፃራሪ ሃይላት በላይ ስለሆነ ።

ይህንን ካለ  በኋላ ወደ ምዕራፍ 9 ይገባል ። ይህንን ማለቱ ግን ለተደራሲያኑ ጆሮ ጥያቄ ይፈጥራል ። ይህም ጥያቄ ምዕራፍ 9:1 ነው ። ይህንን ጥያቄ በቀጥታ በምዕራፍ 9 ባናገኝም ነገርግን በሚመልሰው መልስ ላይ ተመስርተን ጥያቀውን ማግኘት እንችላለን ። ይህም ጥያቄ ታዲያ አንተ እንደምትለው የእስራኤል ህዝብ በእግዚአብሔር ከተመረጠች ለምን እስከ ክብር አልደረሰችም ? የክርስቶስ ፍቅር ብርቱ ከሆነ የእስራኤል ህዝብ ለምን ወደቁ ማለትም እግዚአብሔር የጠራቸውን እስከ ክብር የሚያደርስ ከሆነ- የእስራኤ ህዝብ ለምን አሁን ከክርስቶስ ተለይታ ወደቀች?  የሚለው ነው ።

እስራኤል ይህ መልዕክት በሚፃፍበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጥበቃ ውጪ ሆና የነበረችበት ጊዜ ነው ። ማለትም በዚህ ጊዜ እስራኤል በገዛ ሀገሯ ባርያ የሆነችበት ጊዜ ነው ። እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ሲሆን እስራኤል ታሸንፋለች ድንበሯ ይጠበቃል ጥሩ ንጉስ ይኖራቸዋል ወዘተረፈ ...። አሁን ግን በተገላቢጦሹ እየሆነ ነው ። እንኳን ጠላቶቻቸውን ሊያሸንፉ ይቅር እና በጠላቶቻቸው ተማርከው ባርያ የሆኑበት ወቅት ነበር ። ይህ ደግሞ እስራኤላውያን እንደሚያስቡት የእግዚአብሔር ፍርድ ምልክት ነው ። ይህ ባርነት ባርነት ብዙ Implications አለው ። ከእግዚአብሔር መለየታቸውና እግዚአብሔር ህዝቡን እንደተዋቸው ማሳያ ነው ። — ሮሜ 3፥5 (አዲሱ መ.ት) ።“የእኛ ዐመፃ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አጒልቶ የሚያሳይ ከሆነ፣ ምን ማለት እንችላለን? እንደ ሰው ለመከራከር ያህል እግዚአብሔር በእኛ ላይ ቍጣውን ማምጣቱ ትክክል አይደለም ሊባል ነውን? እንደ ሰው ሲታሰብ ማለቴ ነው።”

ለእዚህ ጥያቄ ጳውሎስ መልስ መስጠት ይጀምራል ።

እስራኤል አሁን ተጥላ ያለችው እግዚአብሔር ቃልኪዳኑን ስላጠፈ ሳይሆን እግዚአብሔር ከሁሉም የእስራኤል ህዝብ ጋር ኪዳን ስለሌለው ነው የሚለውን Argument ያስቀምጣል ።  ሮሜ 9 (አዲሱ መ.ት) ። ⁶ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ተሽሯል ማለት አይደለም፤ ከእስራኤል የተወለደ ሁሉ እስራኤላዊ አይደለምና።  ⁷ ከአብርሃም ዘርም ስለሆኑ፣ ሁሉም ልጆቹ አይደሉም፤ ይልቁንስ፣ “ትውልድህ በይሥሐቅ በኩል ይጠራልሃል” እንደ ተባለው ነው።  ⁸ ይህም ማለት የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት የሥጋ ልጆች አይደሉም፤ ነገር ግን የአብርሃም ልጆች የተባሉት የተስፋው ልጆች ናቸው።

ይህንን ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ማብራራት ይጀምራል ። ከአብርሃም እስማኤል እና ይስሐቅ ቢወለዱም እግዚአብሔር የመረጠው እና ቃል የገባለት ለይስሐቅ ነው ይለናል። ቃል ከተገባለት ይስሐቅ እንኳን ያዕቆብ እና ኤሳው ቢወለዱም እግዚአብሔር ቃልኪዳን የገባው ለሁለቱም ሳይሆን ለመረጠው ለያዕቆብ ነው ። ድሮም ቢሆን እግዚአብሔር በስጋ እስራኤል ከሆኑት ሁሉ ጋር የቃል ኪዳን ውል የለውም ። ስለዚህ አሁን ላይ እስራኤል የወደቀች ብትሆን እግዚአብሔር ቃልኪዳኑን ስላጠፈ ሳይሆን ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን ስለሌለው ነው ። እግዚአብሔር ቃል ለገባለት አካል ታማኝ በመሆኑ እስከ ፍፃሜ ያደርሳል ። ስለዚህ እግዚአብሔር ታማኝነቱ ለመረጣቸው ሰዎች ነው ።

**– ከቁጥር 25-29** እግዚአብሔር ምርጫ ያደረገው ከአህዛብም ጭምር ነው ። መሉ በሙሉ የእስራኤል ህዝብ

አልተመረጠም ። እንዲሁም መሉ በሙሉ አህዛብም አልተተዉም ። ከእስራኤል ቅሬታዎች ድነዋል ። እንዲሁም ከአህዛብ ድነዋል ። **– ቁጥር 30-31 (አ.መ.ት) ³⁰ እንግዲህ ምን እንበል? በእምነት የሆነውን ጽድቅ፣ ለጽድቅ ያልደከሙት አሕዛብ አገኙት፤ ³¹ ነገር ግን የጽድቅን ሕግ የተከታተሉት እስራኤል አላገኙትም። ይህ ሀሳብ አስቀድሞ "እንግዲህ ምሕረት ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም፥ ከሚምር ከእግዚአብሔር ነው እንጂ።"** ይህ በቁጥር 16 የተገለፀውን ሀሳብ የሚያብራራ ነው ። ማለትም ምህረት ለወደደም ለሮጠም አይደለም የሚለውን ሀሳብ በግልጽ የሚያመለክት ነው ።

## ምዕራፍ 10

ይህ ምዕራፍ በዋናነት እግዚአብሔር የመረጣቸው ሰዎች መገለጫቸው ፣ ወይም እግዚአብሔር የጠራቸውን የሚያፀናበትን መንገድ በግልጽ ያብራራልናል ። ይህን ለመረዳት አስቀድሞ እግዚአብሔር ያልመረጣቸው ሰዎች መገለጫዎች ምንድናቸው የሚለውን እንመልከት ።

– ሮሜ 10 (አዲሱ መ.ት) ። ¹ ወንድሞች ሆይ፤ ስለ እስራኤላውያን የልቤ ምኞት፣ እግዚአብሔርንም የምለምነው እንዲድኑ ነው። ² ለእግዚአብሔር ቀናተኞች እንደሆኑ ስለ እነርሱ መመስከር እችላለሁና፤ ቅናታቸው ግን ከዕውቀት የተነሣ አይደለም። ³ ከእግዚአብሔር የሚመጣውን ጽድቅ ሳላወቁና የራሳቸውን ጽድቅ ለመመሥረት ስለ ፈለጉ፣ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም።

1ኛ እግዚአብሔር የመረጠውን የደህንነት መንገድ አይቀበልም ። ይህ መንገድ ደግሞ እግዚአብሔር በክርስቶስ የገለጠውን እውነተኛ መንገድ Reject  ማድረግ ነው ።

2ኛ ለመዳን የራሳቸውን መንገድ ማዘጋጀታቸው  ነው ። እግዚአብሔር እነርሱን ለማዳ የመጣበት መንገድ እና እነርሱ እግዚአብሔር እንዲያድናቸው የሚጠብቁት መንገድ የተለያየ ሆኗል ።

**– እግዚአብሔር የጠራቸው ሰዎች መገለጫዎች !**

1ኛ, እግዚአብሔር ለደህንነት የመረጠውን ብቸኛውን መንገድ ኢየሱስን የሚቀበሉ ናቸው ።

2ኛ, ሌላ የደህንነትን መንድ የማይፈልጉ ናቸው ። በአጠቃላይ እግዚአብሔር የመረጠው ከእግዚአብሔር ጋር በትብብር የሚቆም እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር በተቃራኒ የሚቆም አይደለም ። እግዚአብሔር ህዝብን በዚህ መንገድ ያፀናቸዋል።

# ምዕራፍ 11

ይህ ምዕራፍ አስቀድሞ በምዕራፍ 8 የጀመረውን ሀሳብ በማስታወስ ይጀምርና ፡ የጀመረውን ሀሳብ በመጠቅለል ይጨርሳል ። — ሮሜ 11፥1 (አዲሱ መ.ት) ። "እንግዲህ እግዚአብሔር ሕዝቡን ተዋቸውን? ብዬ እጠይቃለሁ፤ በፍጹም!

ይህ የጳውሎስ ጥያቄው እና መልሱ የሚነግረን እስካሁን ጳውሎስ እያብራራ ያለው ነገር እግዚአብሔር ህዝቡን እንደ ማይተው መሆኑን እንድንረዳ ያደርገናል ። እግዚአብሔር የጠራቸውን ወይንም ህዝቡ የሆኑትን በፍፁም የማይተው ታማኝ አምላክ መሆነን ነው ። ስለዚህ እግዚአብሔር የእኔ ያላቸውን ህዝቦች እስከፍፃማሜ ያደርሳሱ።

በመቀጠል እስካሁን ያቀረበውን ሙግት ወደ መደምደም ይመጣል ።  — ሮሜ 11፥7 (አዲሱ መ.ት) ።

“እንግዲህ ምንድን ነው? እስራኤል አጥብቀው የፈለጉትን አላገኙትም፤ የተመረጡት ግን አገኙት፤ የቀሩትም ልባቸው ደነደነ፤” ከዚህ ቁጥር በዋናነት ሶስት ነገሮችን እንረዳለን ።

**1ኛ, በስጋ ከአብርሃም የተወለዱ እስራኤላውያን ደህንነትን ስለፈለጉ አላገኙም ።** ይህም ማለት አስቀድሞ ምህረት ለወደደም ለሮጠም አይደለም ። ከሚምር ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው የሚለውን ሀሳብ እንዴት በእስራኤል እንደተፈጸመ የሚያሳይ ነው ።

**2ኛ, የተመረጡት ግን አገኙ የሚለው፦ እግዚአብሔር ለመረጣቸው የገባውን ተስፋ የሚፈፅም አምላክ መሆኑን የሚያሳይ ነው ።** ይህም በምዕራፍ 8 የመረጣቸውን አፀደቃቸው - ያፀደቃቸውን አከበራቸው የሚለውን የሚገልጽ ነው ።

**3ኛ, እግዚአብሔር ያልመረጣቸው የክብሩ ተካፋይ አይሆኑም ።** ይህም በምዕራፍ 9:1-6

**– ኃጢአት ብንሰራስ ?**

— 1ኛ ዮሐንስ 2፥1 (አዲሱ መ.ት) ። “ልጆቼ ሆይ፤ ይህን የምጽፍላችሁ ኀጢአት እንዳትሠሩ ነው፤ ነገር ግን ማንም ኀጢአት ቢሠራ፣ በአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፤ እርሱም ጻድቁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።” ይህ በሁለቱም በኩል ለሚነሳው ውጥረት በቂ መልስ አለው ።

1ኛ,ስለዳንን ኃጢአት መስራት ተፈቅዷል? ለሚለው ጥያቄ በፍፁም ነው መልሱ ። 2ኛ, ኃጢአት ስንሰራ ድነታችንን እናጣለን? ለሚለው ጥያቄም በፍፁም ነው ። መልሱ በአብ ዘንድ ጠበቃ አለን ነው መልሱ ።

ይህንን በተለይም በጴጥሮስ ህይወት እንመለከታለን ። –ሉቃስ 22 ³¹ ጌታም፦ ስምዖን ስምዖን ሆይ፥ እነሆ፥ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ ³² እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና አለ።

በቁጥር 31 ላይ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ የሚለውን Plural አድርጎ ሲገልፅ - በቁጥር 32 ላይ ደግሞ ኢየሱስ እምነትህ እንዳይጠፋ ስለአንተ አማለድሁ በማለት singular ያደርገዋል ።

ሰይጣን እንደ ስንዴ አብዝቶ ሊያበጥራቸው ወደደ ብሎ plural አድርጎ ሲገልፅ በይሁዳ እና ጴጥሮስን መሆኑ ግልጽ ነው ። አስቀድሞ በቁጥር 22 ስለይሁዳ ተናግሮ ነበር ።– **ሉቃስ 22፥21 (አዲሱ መ.ት) ። “ነገር ግን እሳልፎ የሚሰጠኝ ሰው እጅ በማእድ ከእኔ ጋር ናት።”** ጴጥሮስ በእግዚአብሔር የተመረጠ በመሆኑ እምነቱ አልጠፋም ። በኢየሱስ ምልጃ እንደገና ተመልሷል ። ይሁዳ ግን የጥፋት ልጅ ስለነበር አልተመለሰም ። የእግዚአብሔር የሆኑቱ እንዳይጠፉ የክርስቶስ ምልጃ ዋስትና ነው ። በክርስቶስ ምልጃም የምናምንበት አንዱ ምክንያት ለዘለአለም ዋስትናችን ነው ።

በክርስቶስ ምልጃ እያመነ ድነቴ ይጠፋል ብሎ እንደሚያምን ሰው አሳዛኝ ሰው የለም ! በመሰረቱ የክርስቶስን ምልጃ ሲያምን ምን ብሎ ነው ያመነው? ሎተሪ ይደርሰኛል ብሎ ነው ያመነው ? ወይንስ በኃጢአት ሰዝል ከኃጢአቴ ሊያወጣኝና ወደ ፀጋው ዙፋን በእምነት እንድቀርብ ያደርገኛል ብሎ ነው የሚያምነው ?

## ከሰነ እምክንዮ እንፃር

ይህንን ከ በ Syllogism እንመለክት ። Major premise, Minor premise and Conclusionኑን እንመልከት ። 1ኛ, የድነታችን መሰረት የእግዚአብሔር ፍቅር ነው ! የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊ ነው ! ስለዚህ ድነት ዘላለማዊ ነው ! ሰው ከዳነ በኋላ ሊጠፋ ይችላል ማለት የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊ አይደለም ማለት ነው !

2ኛ, ዘለአለም ከሚለው የቃል ትርጉም ተነስተን ሰው ድነቱን ሊያጣ አይችልም ወይንም በድነቱ ፀንቶ መኖር ይችላል ማለት እንችላለን ። ዘላለም ማለት በራሱ የማይቋረጥ ማለት ነው ። ድታችን የሚቋረጥ ከሆነ የተቀበልነው ህይወት ዘላለማዊ አልነበረም ማለት ነው ።

ፅድቅ በእምነት ብቻ የሚለውን ተቀብለን የቅዱሳንን ፅናትን የማንቀበል ከሆነ Contradiction ውስጥ ገብተናል ። ፅድቅ በእምነት ብቻ ስንል በማመናችን ብቻ ያለእኛ ተሳትፎ ወደ እግዚአብሔር ቀርበናል በመቅረብም እንቀጥላለን ማለት ነው ። ይህንን ካመንን በኋላ በስራችን ድነትን እናጣለን ደግሞም ድነታችንን በስራ እናስቀጥላለን ብሎ ማለት ተቃርኖ ውስጥ ያስገባናል ።

– ይሁዳ 1 (አዲሱ መ.ት) ። [24] እንዳትወድቁ ሊጠብቃችሁና ያለ ነቀፋና በደስታ በክብሩ ፊት ሊያቀርባችሁ ለሚችለው፣ [25] እርሱ ብቻ አዳኛችን ለሆነው አምላክ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከዘመናት ሁሉ በፊት፣ አሁንና እስከ ዘላለምም ድረስ ክብር፣ ግርማ፣ ኀይልና ሥልጣን ይሁን፤ አሜን።

**– በስተመጨረሻ በቅዱሳን ፅናት ለማያምኑ ሰዎች አንድ ጥያቄ እንጠይቅ ?**

አንድ ሰው በክርስቶስ አምኖ ከሆነ ሰው ጋር እየተጣላ ሳለ በተቃራኒው አካል ተተኩሶበት ተገለ ። ስለዚህ ይህ ሰው የት ነው የሚገባው ?

## መክበር (Glorification)

**the golden chain of salvation** (**የድነት ወርቃማ ሰንሰለት)** የሚባለው ተከታታይ ደረጃዎች በድነት ሂደት ውስጥ የሚያበቃው በአማኞች መክበር ነው። በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰው በንፅህና ፣ በውድቀት ፣ በፀጋ እና በክብር በስፊው ተብራርቶ እናገኛለን ። የሰውን መዳረሻውን ወይንም መጨረሻውን ለመረዳት አስቀድሞ መነሻውን ወይንም መጀመሪያውን መመልከት ጥሩ ነው ።

### – ሰው በንፅህና

ሰው በንፅህና እጅግ የከበረ ፍጥረት ነበር ። ሰው ከውድቀት በፊት የነበረውን ክብር ብንመለከት እጅግ ጠቃሚ ነው ። ሰው በእግዚአብሔር ሲፈጠር ከፍጥረታት ሁሉ እጅግ የከበረ ሰፍራ የተሰጠው ፍጡር ነበር ። እግዚአብሔር በመልኩና በአምሳሉ ከመፍጠሩም ባለፈ በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ገዢ እና ባለቤት አድርጎት ነው የፈጠረው ። ይህንን በመዝሙር መፅሐፍ ምዕራፍ 8 ተብራርቶ እናገኘዋለን ። መዝሙር ምዕራፍ 8 ላይ የሚጠቀሱ ሰው ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ላይ ያለው ሰው ነው ። ማለትም ሰው አስቀድሞ ሲፈጠር የነበረበትን ሁኔታ የሚያወራ መፅሐፍ ነው ።

– መዝሙር 8 (አዲሱ መ.ት) ። [1] እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፤ ስምህ በምድር ሁሉ ላይ ምንኛ ግርማዊ

ነው! ክብርህ ከሰማያት በላይ፣ ከፍ ከፍ ብሎአል። 2 ከልጆችና ጡት ከሚጠቡ ሕፃናት አፍ፣ ምስጋናን አዘጋጀህ፤ ከጠላትህ የተነሣ፣ ባላንጣንና ቂመኛን ጸጥ ታሰኝ ዘንድ። 3 የጣቶችህን ሥራ፣ ሰማያትህን ስመለከት፣ በሰፍራቸው ያኖርሃቸውን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ሳይ፣ 4 በሐሳብህ ስፍራ ትሰጠው ዘንድ ሰው ምንድን ነው? ትጠነቀቅለትም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድን ነው? 5 ከመላእክት በጥቂት አሳነስኸው፤ የክብርንና የሞገስን ዘውድ አቀዳጀኸው። 6 በእጆችህ ሥራ ላይ ሾምኸው፤ ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛህለት፤ 7 በጎችንና ላሞችን ሁሉ፣ የዱር አራዊትንም፣ 8 የሰማይ ወፎችንና፣ የባሕር ዓሦችን፣ በባሕር ውስጥ የሚርመሰመሱትንም ሁሉ አስገዛህለት። 9 እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፤ ስምህ በምድር ሁሉ ላይ ምንኛ ግርማዊ ነው!

ቁጥር 1 ላይ ቃላት በጣረው መልኩ ስለ እግዚአብሔር Majesty ይናገራል ።**<u>ምንኛ ግርማዊ ነው ፣ ከፍ ከፍ ብሎአል</u>** የሚሉ ቃላት እየተጠቀመ እግዚአብሔር ወደር የሌለው በግርማው አስገራሚ አምላክ መሆኑን ያመለክታል ።

**2 ከልጆችና ጡት ከሚጠቡ ሕፃናት አፍ፣ ምስጋናን አዘጋጀህ፤ ከጠላትህ የተነሣ፣ ባላንጣንና ቂመኛን ጸጥ ታሰኝ ዘንድ።** በግርማ እና ሞገስህ Already አንተ እኮ እጅግ የከበርክ ነህ ብሎት ነበር በቁጥር 1 ። አሁን ደግሞ ከህፃናት ምስጋና ለመቀበል መምረጥህ እጅግ አስገራሚ ነው እያለ ይደነቃል ። ህፃናት የሚለው የሰው ፍጥረትን ለመግለጽ ነው ።

ለምንድን ከሰዎች መስጋናን መቀበል አስገራሚ ነገር የሆነው ? ይህንን በቁጥር ሶስት ይነግረናል ።

**3 የጣቶችህን ሥራ፣ ሰማያትህን ስመለከት፣ በሰፍራቸው ያኖርሃቸውን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ሳይ፣4 በሐሳብህ ስፍራ ትሰጠው ዘንድ ሰው ምንድን ነው? ትጠነቀቅለትም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድን ነው?** ቁጥር 3 ሌሎች ፍጥረትን ስላየ ነው የተገረመው ። በጣም ግዙፍ የሆነውን ፍጥረት ተመልክቼ በንፅፅር ሰውን ስመለከት ታሰበው ዘንድ ሰው ምንድነዉ የሚለው ጥያቄ በዳዊት ላይ ጫረበት ።

**5 ከመላእክት በጥቂት አሳነስኸው፤ የክብርንና የሞገስን ዘውድ አቀዳጀኸው።** መላዕክት የሚለው የዕብራይስጡ ቃል ኤሎሂም ነው ። ይህ ቃል ለመላዕክትም ሆነ ለአምላክ ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው ። ስለዚህ አምላክ እንበለው ወይንስ ሰው ? አምላክ ነው የሚሉት ንፅፅሩ አምላክ ፍጥረት እና ሰው ስለሆነ ኤሎሂም የሚለውም አምላክ ለሚለው መሆን አለበት ይላሉ ። እኔ ግን መላእክት ለሚለው ቢገባ የተሻለ ነው ።

ይህንን ሲል ግን የሰዎች እና የመላዕክት ንፅፅር ከማንነት አንፃር ሳይሆን ከተሰጣቸው ኃላፊነት አንፃር ነው የቀረበው። መላዕክት ከሰዎች የሚበልጡበት ነገር አለ ሰዎችም ከመላዕክት የሚበልጡት ነገር አለ ። ለምሳሌ መላዕክት ከሰዎች በኃይል ይበልጣሉ ። **— 2ኛ ጴጥሮስ 2፥11 (አዲሱ መ.ት) ። “<u>ነገር ግን መላእክት ከእነርሱ ይልቅ ብርቱና ኀያል ሆነው ሳሉ</u>፣ በጌታ ፊት በእነርሱ ላይ የስድብ ቃል አይሰነዝሩም።”**

በተቃራኒው ሰዎች ደግሞ ከመላዕክት በስልጣን ይበልጣሉ ። ደግሞ ይህንን የከበረውን ሰው አክሊል የተሰጠውን ፣ ከፍተኛ ሰፍራ የተሰጠውን ሰው ለጥቂት ጊዜ ከመላዕክት አሳነሰው ። የሰባ ሊቃናቱ ትርጉም ለጥቂት ጊዜ ብሎ ነው የተረጎሙት ። ለጥቂት ጊዜ የሚለው የውድቀትን ጊዜ የሚያመለክት ይመስላል ። በኃጢአት ምክንያት ፍጥረት ከ order ወደ des order እንደመጣ እናውቀዋለን ። ይህንን **ከጠላትህ የተነሣ፣ ባላንጣንና ቂመኛን ጸጥ ታሰኝ ዘንድ።** በሚለው መመልከት እንችላለን ስለ ውድቀት እያወራ እንደሆነ ።

ደግሞም ሰው ከውድቀት በፊት በእግዚአብሔር ገነት ውስጥ ነበር የሚኖረው መላዕክት ግን የገነትን በሩን ነበር

የሚጠብቁት ። ከውድቀት በኃላ ሰው ከገነት ተባሮ ወደ ገነት እንዳይገባ የሚከለክሉት ሁለቱ ኪሩቤሎች ናቸው ። ደግሞም የዳንኤልን መፅሐፍ ከተመለከትን ዳንኤል በአንበሶች ጉድጓድ ተጥሎ በነበረ ጊዜ የነበረው ሁኔታ ይህንን በእጅጉ የሚገልጽ ነው ። – ዳንኤል 6 (አዲሱ መ.ት) ። [19] በማለዳም ገና ጎሕ ሲቀድ፤ ንጉሡ ተነሥቶ ወደ አንበሶቹ ጒድጓድ እየተጣደፈ ሄደ። [20] ወደ ጒድጓዱም ቀርቦ በሐዘን ድምፅ ዳንኤልን፣ “የሕያው አምላክ አገልጋይ ዳንኤል ሆይ፤ ሁል ጊዜ የምታመልከው አምላክህ ከአንበሶቹ ሊያድንህ ችሎአልን?” ብሎ ተጣራ። [21] ዳንኤልም እንዲህ ብሎ መለሰ፤ “ንጉሥ ሆይ፤ ለዘላለም ንገሥ፤ [22] ንጉሥ ሆይ፤ በፊቱ ቅን ሆኜ ስለ ተገኘሁ፣ በአንተም ፊት በደል ስላልተገኘብኝ፣ አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶቹን አፍ ዘጋ፤ እነርሱም አልጐዱኝም።”

አስቀድሞ ከውድቀት በፊት ሰው በእንሰሳት ላይ ስልጣን ነበረው ። ነገርግን በውድቀት ጊዜ ይህንን ስልጣን አጥቶ ለእርዳታ መላዕክት አስፈልጎት ነበር ። ስለዚህ ለጥቂት ጊዜ አነሰ የሚለው ይህንን የሚያመለክት ነው ።

ደግሞም ለጥቂት ጊዜ የሚለው የሰው ልጅ ወደ ክብሩ የሚመለሰበት ጊዜ እንዳለም አቅጣጫ የሚጠቁም ነው ። ይህ የውድቀት ዘመን የሚያበቃበትና ሰው ወደ ክብሩ የሚመለሰበት ዘመን እንደሚመጣ ዳዊት ተረድቷል ። ነገርግን አማኞች አሁን የሚጠብቃቸው ክብር ቀድሞ ከነበረው ክብር እጅግ ከፍ ያለ ነው ።

እግዚአብሔር አማኞችን በክርስቶስ በኩል ሲያከብራቸው አዳም ቀድሞ ወደነበረበት ሁኔታ ብቻ አልመለሰውም ። አዳም ቢታዘዝ ኖሮ የሚያገኘውን ሽልማት ነው የሰጣቸው ። ይህም በክርስቶስ መታዘዝ መክኒያት ነው ። — **– ራእይ 2፥7 (አዲሱ መ.ት) ። “መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን፣ ጆሮ ያለው ይስማ፤ ድል ለሚነሣ በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ አደርገዋለሁ።”**

ይህ በደንብ የሚገባን አዳም ያጣውን ነገር ስንመለከት ነው ። – ዘፍጥረት 3 (አዲሱ መ.ት) [22] ከዚያም እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም)፣ “ሰው መልካምንና ክፉውን ለይቶ በማወቅ ረገድ አሁን ከእኛ እንደ አንዱ ሆኗል፤ አሁን ደግሞ እጁን ዘርግቶ ከሕይወት ዛፍ ቀጥፎ እንዳይበላ፣ ለዘላለምም እንዳይኖር ይከልከል” አለ። [23] ስለዚህ የተገኘበትን ምድር እንዲያርስ፣ እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ሰውን ከዔድን የአትክልት ስፍራ አስወጣው፤ [24] ሰውንም ካስወጣው በኋላ፣ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና በየአቅጣጫው የምትገለባበጥ ነበልባላዊ ሠይፍ ከዔድን በስተ ምሥራቅ አኖረ። አዳም የህይወትን ዛፍ እንዳይበላ ተከልክሏል ነገርግን በክርስቶስ በኩል ለሆኑት ይህ ተችሏል ።

## – የመክበር ከፍታ

መክበር የሚለው ሃሳብ ከኃጢአት መዳን እና ወደ ሰማይ ከመሄድ ይበልጣል! ጳውሎስ በሮሜ 8፥29 ላይ “እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናቸው፤ ይኸውም ከብዙ ወንድሞች መካከል እርሱ በኵር እንዲሆን ነው።” — ሮሜ 8፥29 (አዲሱ መ.ት) ። ይላል። አስቀድሞ የተወሰነው ተጠርቷል፣ ጸድቋል እና በመጨረሻም ክብር አለው። **ይህ “መክበር” ከልጁ ምስል ጋር ተመሳሳይ ነው።**

እግዚአብሔር ምዕመኑን ያከብራል ማለት ‘አማኙ ታልቅ ይሆናል’ ማለት አይደለም ወይም ነጭ ልብሰ ለብሶ በሰማይ ይቀመጣል ማለት አይደለም። አማኝ ክርስቶስን እንዲመስል ይደረጋል ለዓለም የእግዚአብሔርን ክብር ያሳያል ማለት ነው። ይህ የመዳን የመጨረሻ ግብ ነው።

— 1ኛ ዮሐንስ 3፥2 (አዲሱ መ.ት) ። “ወዳጆች ሆይ፤ እኛ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ወደ ፊት ምን እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ እናየዋለንና፣ እርሱን እንደ ምንመስል እናውቃለን።”

የአማኞች ትልቁ ተስፋ ክርስቶስን መምሰል እንጂ እዚህ ምድር ላይ ስኬት ብለው የሚያስቡትን ነገር ያለምንም መከልከል በመንግስተ ሰማያት ማግኘት አይደለም ። ደግሞም ይህ ተጨባጭና የተረጋገጠ ተስፋ ነው ። ይህንን **<u>እርሱን እንደ ምንመስል እናውቃለን።"</u>** በሚለው መረዳት እንችላለን ። ይህ ማለት በእዚያኛው አለም በጎ ነገሮች ሁሉ አያገኙንም ማለት አይደለም ።

– ራእይ 21 (አዲሱ መ.ት) ። [1] ከዚህ በኋላ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አየሁ፤ የመጀመሪያው ሰማይና የመጀመሪያዪቱ ምድር ዐልፈዋልና፤ ባሕርም ከእንግዲህ ወዲህ አይኖርም። [2] ቅድስቲቱ ከተማ፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለባሏ እንደ ተዋበች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ። [3] ደግሞም እንዲህ የሚል ታላቅ ድምፅ ከዙፋኑ ሲወጣ ሰማሁ፤ "እነሆ፤ የእግዚአብሔር ማደሪያ በሰዎች መካከል ነው፤ እርሱ ከእነርሱ ጋር ይኖራል፤ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ፤ እግዚአብሔር ራሱም ከእነርሱ ጋር ይኖራል፤ አምላካቸውም ይሆናል። [4] እንባን ሁሉ ከዐይናቸው ያብሳል፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሞት ወይም ሐዘን ወይም ልቅሶ ወይም ሥቃይ አይኖርም፤ የቀድሞው ሥርዐት ዐልፎአልና።" [5] በዙፋኑ ላይ የተቀመጠውም፣ "እነሆ፤ እኔ ሁሉን ነገር አዲስ አደርጋለሁ" አለ፤ ደግሞም፣ "ይህ ቃል የታመነና እውነት ስለ ሆነ ጻፍ" አለ። [6] እንዲህም አለኝ፤ "ተፈጸመ፤ አልፋና ዖሜጋ፣ የመጀመሪያውና የመጨረሻው እኔ ነኝ፤ <u>ለተጠማ ከሕይወት ውሃ ምንጭ ያለ ዋጋ እሰጣለሁ</u>።

በእዚህ መከራና ሀዘን ለቅሶ የለም የሚለው በእዚህ መከራና ለቅሶ ሀዘን ስላለ ነው ። በእዚህ እንባ ሁሉ የሚታበስላቸው በእዚህ ለሚያነቡ ነው ። **ሪቻርድ ፊሊፕስ እንደገለጸው "መጽሐፍ ቅዱስ የሚደመደመው የተከበረች ከተማ በሆነችው አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ሲሆን የአምላክ ሕዝቦች በክብር ለዘላለም የሚኖሩባትን ሥዕል በማሳየት ነው።**

## – መክበራችን እዚህ ምድር ላይ ካሉት ከሁሉ ነገር ይልቃል

– ሮሜ 8 (አዲሱ መ.ት) ። [17] ልጆች ከሆን ወራሾች ደግሞ ነን፤ የክብሩ ተካፋዮች እንሆን ዘንድ በርግጥ የመከራው ተካፋዮች ብንሆን፣ የእግዚአብሔር ወራሾች፣ ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን። [18] የአሁኑ ዘመን ሥቃያችን ወደ ፊት ሊገለጥ ካለው ለእኛ ከተጠበቀልን ክብር ጋር ሲነጻጸር ምንም እንዳይደለ እቈጥራለሁ። [19] ፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ በናፍቆት ይጠባበቃል።

የእግዚአብሔር ወራሾች መሆን ፣ ክርስቶስ የወረሰውን መውረስ ነው የመጨረሻው መዳረሻችን ። እግዚአብሔር አዳኝ በሆነ መንገድ አማኞችን ሲቤዣቸው ከክርስቶስ ጋር አንድ ስለሚያደርጋቸው፣ በክርስቶስ ያሉ በረከቶች ሁሉ እንደሚካፈሉ ዋስትና ተሰጥቷቸዋል። እነዚያ እግዚአብሔር በጊዜ ያጸደቃቸው ለዘለዓለም ያከብራል ። ኢየሱስ ከሙታን በመነሣቱ በሰውነቱ እንደ ከበረ እንዲሁ በእምነት ከእርሱ ጋር የሚተባበሩት ሁሉ የዚያው ክብር ተካፋዮች ይሆናሉ። የቤዛነት በረከቶችን ሁሉ ተግባራዊ ይሆንላቸዋል ።

የሚመጣው አለምና የአሁን አለም ለንፅፅር የሚቀርብ እንዳልሆነ በጳውሎስ የቃላት አጠቃቀም መረዳት እንችላለን ። **[18] የአሁኑ ዘመን ሥቃያችን ወደ ፊት ሊገለጥ ካለው ለእኛ ከተጠበቀልን ክብር ጋር ሲነጻጸር ምንም እንዳይደለ እቈጥራለሁ።** ጳውሎስ ይህንን የሚለው እንደ እኛ አይነት ተራ መከራ ገጥሞት አይደለም ።

– 2ኛ ቆሮንቶስ 11 (አዲሱ መ.ት) ። [22] እነርሱ ዕብራውያን ናቸውን? እኔም ነኝ፤ እስራኤላውያን ናቸውን? እኔም ነኝ፤ የአብርሃም ዘር ናቸውን? እኔም ነኝ። [23] የክርስቶስ አገልጋዮች ናቸውን? እንደ እበደ ሰው ልናገርና እኔ እበልጣቸዋለሁ፤ ደግሞም ብዙ ጊዜ በሥራ ደክሜአለሁ፤ ብዙ ጊዜ ታስሬያለሁ፤ ብዙ ጊዜ ተገርፌአለሁ፤ ብዙ

ጊዜ ለሞት ተቃርቤአለሁ። [24] አይሁድ ለአርባ ጅራፍ አንድ የቀረው አምስት ጊዜ ገርፈውኛል። [25] ሦስት ጊዜ በዱላ ተደብድቤአለሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወግሬአለሁ፤ ሦስት ጊዜ የመርከብ አደጋ ደርሶብኛል፤ አንድ ሌሊትና ቀን በባሕር ላይ አድሬአለሁ፤ [26] ብዙ ጊዜ በጕዞ ተንከራትቻለሁ፤ ደግሞም ለወንዝ ሙላት አደጋ፣ ለወንበዴዎች አደጋ፣ ለገዛ ወገኖቼ አደጋ፣ ለአሕዛብ አደጋ፣ ለከተማ አደጋ፣ ለገጠር አደጋ፣ ለባሕር አደጋ እንዲሁም ለሐሰተኞች ወንድሞች አደጋ ተጋልጬ ነበር። [27] ብዙ ጥሬአለሁ፤ ብዙ ደክሜአለሁ፤ ብዙ ጊዜ እንቅልፍ አጥቻለሁ፤ ተርቤአለሁ፤ ተጠምቻለሁ፤ ብዙ ጊዜ ምግብ ሳልቀምስ ኖሬአለሁ፤ በብርድና በራቍትነት ተቈራምጃለሁ። [28] ሌላውን ነገር ሳልቈጥር፣ ዕለት ዕለት የሚያስጨንቀኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሐሳብ ነው።

እኛ የጳውሎስን ያክል እንኳ መከራ አልተቀበልንም ። ነገር ግን እርሱ ያንን ሁሉ መከራ ከሚመጣው ክብር ጋር ሲያስተያይ እንደ ምንም ነገር ይቆጥረዋል ። ጳውሎስ ከፊት ለፊቱ ያለውን አለም ፣ የእግዚአብሔርን መንግስት ተመልክቶ ነው ይህንን ሁሉ መከራ የሚቀበለው ።

ጌታ ኢየሱስም በከባድ ስቃይ ውስጥ ቢያልፍም የሚመጣውን ክብር ተመልኮቶ ሁሉን በትዕግሥት አልፏል ። — ዕብራውያን 12፥2 (አዲሱ መ.ት) ። "የእምነታችን ጀማሪና ፍጹም አድራጊ የሆነውን ኢየሱስን እንመልከት፤ <u>እርሱ በፊቱ ስላለው ደስታ መስቀሉን ታግሦ፣ የመስቀሉንም ውርደት ንቆ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአል።"</u>

ክርስቶስ የሚጠብቀውን ደስታ እየተመለከተ መስቀልን የሚያክል ነገር ታገሰ ፣ እግዚአብሔርም በቀኙ አስቀምጦት አነገሰው ።

**– መቼ ነው የምንከብረው ?**

ክርስቶስ ወደምድር ሲመጣ ።

– ፊልጵስዩስ 3 (አዲሱ መ.ት) ። [19] መጨረሻቸው ጥፋት ነው፤ ሆዳቸው አምላካቸው ነው፤ ክብራቸው በነውራቸው ነው፤ ልባቸው ያረፈው በምድራዊ ነገር ላይ ነው። [20] እኛ ግን አገራችን በሰማይ ነው፤ <u>ከዚያ የሚመጣውንም አዳኝ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በናፍቆት እንጠባበቃለን፤</u> [21] እርሱም ሁሉን ለራሱ ባስገዛበት ኀይል፣ ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል።

እኛ እንኼዳለን ሳይሆን የሚለው የሚመጣ አዳኝ አለ ነው የሚለው ። ይህ አዳኝ ሁሉን ያስገዛበት የራሱ ሀይል አለ። ይህ ኃይል ደግሞ የተዋረደው ስጋችንን በክብር ይለውጠዋል ። የተዋረደ ስጋ የሚለው በዋናነት ሁለት ነገሮችን ሊሸከም ይችላል ። 1ኛ, በኃጢአት የደከመው ፣ ኃጢአት ያዛለው ያስለቸው ሊሆን ይችላል ። 2ኛ, የክርስቶስ በመሆኑ ምክንያት የተሰደደው ፣ የተንገላታው ሊሆን ይችላል ። በሁለቱም መንገድ አማኞች ይከብራሉ ።

**በወንድም ተካልኝ ኃ/ሚካኤል**